# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 120 ታኅሣሥ 30 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ስኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# የኢትዮጵያ

## የዲፕሎማሲ ሳምንት የሀገሪቱን ስኬታማ የዲፕሎማሲ ጉዞ አጉልቶ የሚያሳይ ነው

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ሳምንት የሀገሪቱን ቀጣናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ስኬታማ የዲፕሎማሲ ጉዞ አጉልቶ የሚያሳይ ነው ሲል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ገለጸ፡፡ የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ሳምንት ኤግዚቢሽን ከጥር ሁለት ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ "ከአፍሪካ መዲናነት እስከ ዓለም መድረክ" በሚል መሪ ቃል በሳይንስ ሙዚየም እንደሚከፈትም ተጠቁሟል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ብርቱካን አያና ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት በኢትዮጵያ ሚሲዮኖች በኩል ዜጎችን ያማከለ የዲፕሎማሲ አገልግሎት እንዲረጋገጥ እየተሠራ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ሳምንት የሀገሪቱን ቀጣናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ስኬታማ የዲፕሎማሲ ጉዞ አጎልቶ የሚያሳይ ነው፡፡

ከጥር ሁለት እስከ 24 ቀን 2016 ዓ.ም በሳይንስ ሙዚየም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰናዳው የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ሳምንት ኤግዚቢሽን ብዙ ዓላማዎች እንዳሉት የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታዋ፣ የኢትዮጵያን ያለፉ ዲፕሎማሲያዊ ድሎች እና ተግዳሮቶች ማሳየት፣ ኢትዮጵያ አሁን ያለችበትን ዲፕሎማሲያዊ መንገድ

የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አምባሳደር ብርቱካን አያና






# በ2016

## በመጀመሪያ አምስት ወራት ከ84 ሺህ በላይ የቁም እንስሳት ወደ ውጪ ተልከዋል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 ዓ.ም በመጀመሪያ አምስት ወራት ብቻ ከ84 ሺህ በላይ የቁም እንስሳትን ወደ ውጪ መላክ መቻሉን የንግድ ቀጣናዊ

በ2016 በመጀመሪያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ደብረ ማርቆስ

## ዩኒቨርሲቲ 11 ሺህ ተማሪዎችን ስመቀበል ዝግጅት እያደረገ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በ2016 የትምህርት ዘመን 11 ሺህ ተማሪዎችን ለመቀበል በቂ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አስታወቀ።

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት ይኸይስ አረጉ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ዩኒቨርሲቲው ከጥር ወር ጀምሮ ተማሪዎችን ለመቀበል ሙሉ ዝግጅት እያደረገ ነው። ለዚህም የሀገር ሽማግሌዎች፣ የኃይማኖት አባቶችና ከማኅበረሰቡ የተውጣጡ ግለሰቦች ጋር በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ገንቢ ውይይት አካሂዷል።

ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲውን ልክ እንደቤታቸው እንዲቆጥሩና በቆይታቸውም እንዲደሰቱ ለማድረግ የበኩላችንን እንወጣለን ያሉት ዶክተር ይኸይስ፤ ተማሪዎቹ በአቀባበል ጊዜም ሆነ ትምህርታቸው በሚከታተሉበት ወቅት የመማር ማስተማሩን ሥራ ከሚያውኩ ተግባራት

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በላሊበላ የተከበረው የገና በዓል ተቀዛቅዞ የቆየውን የክልሉን ቱሪዝም ማነቃቃት አስችሏል

## - ለበዓሉ ታዳሚዎች ከ45 በላይ ሆቴሎች አገልግሎት ሰጥተዋል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በቅዱስ ላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት የተከበረው የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓልና የቤዛ ኩሉ ሥርዓት ተቀዛቅዞ የነበረውን የክልሉን ቱሪዝም ማነቃቃት እንዳስቻለ የሰሜን ወሎ ዞን የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን መምሪያ አስታወቀ። በዓሉ ላይ ለተገኙት ከ500 ሺህ በላይ ቱሪስቶች ከ45 በላይ ሆቴሎች አገልግሎት መስጠታቸው ተመላክቷል፡፡

የመምሪያው ኃላፊ ዲያቆን ተፈራ ሰይፉ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዘንድሮው የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓልና የቤዛ ኩሉ ሥርዓት ላይ በተገኙ ጎብኚዎች አማካኝነት በክልሉ የፀጥታ ችግር ምክንያት ተቀዛቅዞ የነበረውን ቱሪዝም ማነቃቃት ተችሏል፡፡

የኮቪድ 19 ወረርሽኝ፣ የሰሜኑ ጦርነትና በክልሉ

በላሊበላ የተከበረው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









# የምክር ቤት አባላቱ በጤናማ ፉክክር ለመዲናዋ ሁለንተናዊ ለውጥ እንደሚተጉ አስታወቁ

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- በጤናማ ፉክክር እና ትብብር ለመዲናዋ ሁለንተናዊ ለውጥ እንደሚተጉ የአዲስ አበባ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አባላት ተናገሩ።

በአዲስ አበባ የሚገኙ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች ዓድዋ ዜሮ ዜሮ ኪሎሜትር ፕሮጀክትን ጨምሮ በከተማችን ተገንብተው አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ትላላቅ ፕሮጀክቶችንና ሰው ተኮር ሥራዎችን ተዘዋውረው ጎብኝተዋል።

በአዲስ አበባ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት የሴቶች ክንፍ ሰብሳቢ እመቤት ቢራራ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የለሚ እንጀራ ፋብሪካ እና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የተገነቡ የመኖሪያ ቤቶች እንዲሁም የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከላት ሰው ተኮር የልማት ፕሮጀክቶች በመሆናቸው የኅብረተሰቡን ኑሮ ለማሻሻል ይረዳሉ።

እነዚህ የልማት ሥራዎች የኅብረተሰቡ በተለያዩ መድረኮች ሲያነሳቸው የነበሩ በመንግሥትና በበጎ



እመቤት ቢራራ

አድራጊዎች ትብብር የተሠሩ መሆናቸውን ያነሱት ሰብሳቢዋ፤ የምናራምዳቸውን ሀሳቦች ለሚዳኘን ሕዝብ እያቀረብን ተፎካካሪነታችንን እናጠናክራለን ብለዋል።

በከተማዋ የመሬት አቅርቦት፣ ለተለያዩ የከተማዋ መሠረታዊ ፍላጎት የበጀት ድጎማ፣ የሥራ እድል የመፍጠር፣ የኑሮ ጫናን የሚያቃልሉና በየወቅቱ ለሚነሱ ማኅበራዊ



አቶ ማሩ ጃኔ

ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት እንደሚገባ ገልጸው፤ በከተማዋ የተሠሩት ሰው ተኮር የልማት ሥራዎች ተጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባ ገልጸዋል።

በአዲስ አበባ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት የአብን የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ማሩ ጃኔ በበኩላቸው፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማውን ነዋሪ የኑሮ ጫና ለማቅለል እየሠራቸው ያሉ ሥራዎች የበርካቶችን ሕይወት እየቀየሩ መሆናቸውን መገንዘባቸውን ገልጸዋል።

የዓድዋ ዜሮ ዜሮ ኪሎሜትር ፕሮጀክትን ጨምሮ በከተማዋ እየተገነቡ ያሉ ታላላቅ ፕሮጀክቶች የከተማዋን ገፅታ ከመቀየር ባሻገር ለትውልድ የሚተላለፉ ሥራዎች መሆናቸውን ተናግረዋል።

በለሚ ኩራ የአረንጓዴ ልማት ሥራዎች እና አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የሚገኘው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የእንስሳት ልማትና ልህቀት ማዕከል መጎብኘታቸውን የጠቀሱት አቶ ማሩ፤ የለሚ ኩራ የአረንጓዴ ልማት ሥራዎች የክፍለ ከተማውን ገፅታ ከመቀየር ባለፈ ለበርካታ ወጣቶች የሥራ ዕድል እንደፈጠረ መገንዘባቸውን ተናግረዋል። ሥራው ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበትም ገልጸዋል።

ከተማዋ፣ ሀገራዊ የልማትና የሰላም ጉዳዮች ላይ መጠላለፍ የበዛበትን የፖለቲካ ባሕል ወደ ትብብርና ፉክክር ለማሳደግ እንደሚሠሩ የገለጹት አቶ ማሩ፤ በጤናማ ፉክክር እና ትብብር ለመዲናዋ ሁለንተናዊ ለውጥ እንተጋለን ብለዋል።



# በክልሉ 10 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል የቡና ምርት ተሰብስቧል

አመለወርቅ ከበደ

አዲስ አበባ፡- በ2016 የምርት ዘመን እስካሁን 10 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል የቡና ምርት እንደተሰበሰ የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ገለጸ።

የቢሮው ምክትል ኃላፊ አቶ መሐመድ ሳኒ ለኢፕድ እንደገለጹት፣ በ2016 ዓ.ም ከክልሉ 11 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል የቡና ምርት ለመሰብሰብ ታቅዶ እስካሁን 10 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ተሰብስቧል።

በምርት ዘመኑ ከሚገኘው የቡና ምርት 75 በመቶ ወይም ሰባት ሚሊዮን ኩንታሉን ለማዕከላዊ ገበያ ለማቅረብ መታቀዱን ጠቅሰው፤ የቡና ምርት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ምርት የማሰባሰብ ሂደቱ ከደጋማ ቦታዎች በስተቀር ተጠናቋል ያሉት አቶ መሐመድ፤ የ2017 የምርት ዘመን የምርጥ ዘር ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል።

በምርጥ ዘር ዝግጅቱ 826 ሺህ ኪሎግራም የቡና ዘር ለማዘጋጀት እቅድ መያዙን አስታውሰው፤ እስካሁን 780 ሺህ ኪሎ ግራም የቡና ዘር መዘጋጀቱን አስረድተዋል።

እንደ ምክትል ኃላፊው ገለጻ፤ የቡና ችግኝ አዘጋጅቶ ለአርሶአደሮች ተደራሽ ከማድረግ አኳያ ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ችግኞችን በማዘጋጀት የመንከባከብ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል።

የቡናምርጥዘርንተደራሽየሚያደርግየመንግሥትም ሆነ የግል አካል ባለመኖሩ በአርሶአደሮችና በምርምር ጣቢያዎች በተወሰነ መጠን እንዲዘጋጅ እየተደረገ መሆኑን አስታውቀዋል።

የቡና ምርታማነትን ከማሳደግ አንጻር ያረጁ ቡናዎችን የመጎንደል ሥራ መጀመሩን ያነሱት አቶ መሐመድ፤ ጎን ለጎን የተፈጥሮ ማዳበሪያ የማዘጋጀት ሥራ እየተከናወነ መሆኑን አመላክተዋል።

የቡና ግብይት ሰንሰለቱን ከማሳጠር አንጻር ሁለት ሄክታርና ከዛ በላይ የቡና ማሳ ያላቸው አርሶአደሮች በቀጥታ ከላኪዎች ጋር ተገናኝተው እንዲሠሩ እየተደረገ መሆኑን ጠቁመው፤ አሠራሩን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ የተሻለ ቅንጅት ይጠይቃል ሲሉ ገልጸዋል።

በክልሉ 18 ዞኖች ቡና የሚመረት ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ 12 ዞኖች በስፋት በቡና ምርት ይታወቃሉ። ጅማ፣ ኢሉ አባቦራ ፣ ምዕራብና ቄለም ወለጋ፣ ጉጂ አካባቢዎች ሰፊ የቡና ምርት የሚገኝባቸው አካባቢዎች መሆናቸውን ጠቁመዋል።

# በክልሉ የተፋሰስ ሥራ አራት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዜጎች ይሳተፋሉ

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በ2016 ዓ.ም የአፈርና ውኃ ጥበቃ ሥራ አራት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዜጎች እንደሚሳተፉ የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ። በአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራው 376 ሺህ 561 ሄክታር መሬት ለማልማት ታቅዷል።

የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አልማዝ ጊዜው (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአማራ ክልል የ2016 ዓ.ም የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራን ለመጀመር የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል።

የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራው በዘጠኝ ሺህ 60 ተፋሰሶች ላይ የሚከናወን ሲሆን፤ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ አራት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዜጎች ይሳተፋበታል ሲሉ አስረድተዋል።


በአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራው 376 ሺህ 561 ሄክታር መሬት የሚለማ ሲሆን፤ 234 ሺህ 118 ሄክታር መሬት በአዲስ መልክ እና 142 ሺህ 443 ሄክታር መሬት ደግሞ በነባር ልማት የተፋሰስ ደረጃውን ለማሳደግ እንደሚሠራ አመላክተዋል።

የተፋሰስ ልማቶች ዘላቂነት እንዲኖራቸውና የማኅበረሰቡን ተጠቃሚነት እንዲያረጋግጡ የተፋሰስ የኅብረት ሥራ ማኅበራት መደራጀታቸውን አስታውቀዋል።

እስካሁን በአፈርና ውሃ ጥበቃ ከሚሳተፉት የኅብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ከ50 በመቶ በላይ የሚሆኑትን ማደራጀት መቻሉን አስረድተዋል።

የሰው ኃይሉን ከማደራጀት በተጨማሪ የልማት መሣሪያዎችን የማሰባሰብ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ጠቁመው፤ በአዲስ፣ በደረጃ ማሻሻልና ጥገና ምን ያህል ሄክታር መሬት እንደሚለማ የመለየትና በማኅበር የተደራጁትን የተፋሰስ አባላት ብቁ የማድረግ ሥራ ይሠራል ብለዋል።

የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራውን ውጤታማ ለማድረግ የባለሙያውን አቅም መገንባት ወሳኝ



ነው ያሉት ዶክተር አልማዝ፤ ሳይንሳዊ የተፋሰስ ልማት ሥራውን በግብርና ባለሙያዎች ብቻ የሚከናወን ባለመሆኑ ቀያሽ አርሶአደሮችን በመምረጥ የማሠልጠን ሥራ እየተሠራ መሆኑን አብራርተዋል።

ለሥልጠና ከተመረጡ 379 ሺህ አርሶ አደሮች መካከል እስካሁን 30 በመቶ የሚሆኑት ሥልጠናቸውን አጠናቀው ለሥራው ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸው፤ የሠለጠኑት ደግሞ በሥራቸው ለአርሶ አደሮችን በቂ ድጋፍ እንዲሰጡ ጥረት እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

ክልል አቀፍ የአፈርና ውኃ ጥበቃ ሥራ እንደየአካባቢው ሥነ-ምሕዳር ሁኔታ ጥር አንድ ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ እንደሚጀመር አስታውቀዋል።

የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ የአፈር መሸርሸርን በመከላከል ምርትና ምርታማነት ለመጨመር፣ የሥራ እድል ለመፍጠር፣ የአየር ብክለትን ለመከላከል እና ሌሎች ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎችን እንደሚያስገኝ ገልጸዋል።

ከዚህ በፊት በተሠሩት የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎችን በቂ ጊዜ ሰጥቶ አለመሥራት፣ የሥራ ጥራት ጉድለትና ሌሎች ውስንነቶች እንደነበሩ አስታውሰው፤ ያለፉት ውስንነቶች በዘንድሮው ዓመት ለማስቀረት ጥረት ይደረጋል ብለዋል።



አቶ አዱኛ በቀለ

# የግጭት መረጃዎችን

## በመተንተን ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ቴክኖሎጂ በሚቀጥለው ዓመት ወደሥራ ይገባል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የግጭት መረጃዎችን በመተንተን ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ሥርዓት በሚቀጥለው ዓመት ወደሥራ እንደሚገባ የሠላም ሚኒስቴር አስታወቀ።

በሠላም ሚኒስቴር የስትራቴጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈፃሚ አቶ አዱኛ በቀለ ለኢፕድ እንደተናገሩት፤ ከጊዜ ወደጊዜ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች እየተስፋፋ የመጣውን ግጭት የመከላከልና የማስተዳደር ሥራዎችን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ለማድረግ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በትኩረት እየተሠራ ሲሆን፤ በዚህም የግጭት መረጃዎችን በመተንተን ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ሥርዓት በሚቀጥለው ዓመት ወደሥራ ይገባል።

ሩት ሶሉሽን የተባለ ተቋም ቴክኖሎጂውን በማልማት ለሠላም ሚኒስቴር ድጋፍ ያደረገ ሲሆን አሁን ላይ ከኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ጋር በመሆን የቴክኖሎጂው ጥንካሬ እየተፈተሸ ይገኛል ብለዋል።

በዚህም የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር በሰጠው የመጀመሪያ ዙር ግብረ መልስ መልካም ምላሾች እንደተገኙና በዚህ ዓመት ቴክኖሎጂውን የመፈተሽና የማጠናከር ሥራው ተጠናቆ በሚቀጥለው ዓመት ወደትግበራ እንደሚገባ አቶ አዱኛ ገልጸዋል።

ቴክኖሎጂው ሲጠናቀቅ የግጭት መረጃ የመሰባሰብ፣ የመተንተንና የምላሽ አሰጣጥ ሥርዓቱን ዘመናዊ በማድረግ በየወቅቱ ለሚከሰቱ ግጭቶች ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ወጥ የአሠራር ሥርዓት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እንደሚዘረጋ አመላክተዋል።

በዚህ ረገድ የተለያዩ ባለ ድርሻ አካላትን ያካተተ የኢትዮጵያ ልዑክ ወደጋና በመሄድ የግጭት ወቅት የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ምን እንደሚመስል ሰፊ የልምድ ልውውጥ ማድረጋቸውን አስታውሰው፤ በመሆኑም በፌደራልና ግጭት በተደጋጋሚ በሚከሰትባቸው ክልሎች ላይ የሁኔታ መከታተያ ክፍሎችን (situation room) የማደራጀት ሥራ ተሠርቷል ነው ያሉት።

እንደ አቶ አዱኛ ገለጻ፤ አሁን ላይ በውስጥ አቅም የለሙ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም መረጃዎች እየተሰበሰቡና ፈጣን ምላሾች እየተሰጡ ሲሆን፤ በዚህ ረገድ በክልሎች የሚገኙ የሁኔታ መከታተያ ክፍሎችንና ሠራተኞቻቸውን የማጠናከር ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ።

በተሠራው የክትትልና ድጋፍ ሥራ የሐረሪ፣ የደቡብ ኢትዮጵያ፣ የደቡብ ምዕራብ ክልሎች በአንጻራዊነት የተሻሉ መሆናቸውን አንስተው፤ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ አፋር፣ ጋምቤላ፣ ሶማሌ፣ ሲዳማ ክልሎች እንዲሁም የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች የተቀመጡ መስፈርቶችን መሠረት አድርገው እየሠሩ እንዳልሆነ መታየቱን ሥራ አስፈፃሚው ጠቁመዋል።

የተቋማቱ መጠናከር በቀጣይ ሲስተሙ ሲዘረጋ ጠንካራ የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ ከወዲሁ እንደሚረዳ ገልጸው፤ ይህንን ለማድረግም የተለያዩ አጋር አካላት ጋር እየተሠራ ነው ብለዋል።

በዚህም ከኮሪያ መንግሥት በተገኘ ድጋፍ በኦሮሚያና ሶማሌ ክልሎች በሚገኙ አስር ወረዳዎች ላይ የሁኔታ መከታተያ ክፍሎችን የማጠናከርና ለባለሙያዎች ሥልጠና የመስጠት ሥራ መከናወኑን ጠቁመዋል።

ከዚህ አንጻር በሩብ ዓመቱ በአጠቃላይ 32 የሚሆኑ የግጭት መረጃዎች ተሰብስበውና ተተንትነው ለሚመለከተው አካል የተላለፉ ሲሆን 21 ግጭቶችን ቀድሞ መከላከል እንደተቻለም አቶ አዱኛ ገልጸዋል።

# የዋጋ ግሽበትን ለመቋቋም የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ተወዳዳሪ ማድረግ ይገባል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ:- በዓለም አቀፍም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚስተዋለውን የዋጋ ግሽበት ለመቋቋም እንደ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ያሉ ተቋማትን ተወዳዳሪና ተፅዕኖ ፈጣሪ ማድረግ እንደሚገባ ተገለጸ። የኅብረት ሥራ ማኅበራት የልማትና እድገት የሪፎርም ንቅናቄ ተካሂዷል።

በመድረኩ የግብርና ሚኒስትር ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) ባስተላለፉት መልዕክት፣ ኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ ብልጽግና ለማምጣት እየተከተለች ካለው የልማት ፖሊሲ አንጻር በዓለም አቀፍም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚስተዋለውን የዋጋ ግሽበት መቋቋም የሚቻለው እንደ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ያሉ ተቋማትን ተወዳዳሪና ተፅዕኖ ፈጣሪ ማድረግ ሲቻል ነው ብለዋል።

ኅብረት ሥራ ማኅበራት የዜጎችን የተናጠል ጉልበት፣ ገንዘብና እውቀት የሚያሰባስቡ ናቸው ያሉት ሚኒስትሩ፣ በመንግሥት የኢኮኖሚ ዘርፍ መካከል የሚፈጠረውን ጉድለት ለመሙላትና የገበያ ሚዛን ለመጠበቅ ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ጠቁመዋል። በዚህም እንደ ሦስተኛ የኢኮኖሚ ዘርፍ ተደርገው የሚወሰዱ ተቋማት መሆናቸውን ገልጸዋል።

በተለይም ኅብረት ሥራ ማኅበራት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ ለውጪ ምንዛሪና ለኢንዱስትሪ ጥሬ እቃ ዋነኛ ምንጭ በመሆን የሚያገለግለውን የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ለማሳደግ የማይተካ ሚና ያላቸው መሆናቸውንም ጠቁመዋል።

ሚኒስትሩ እንዳሉት፣ ማኅበራቱ በግብርና፣ ኢንዱስትሪና አገልግሎት ዘርፎች በመሰማራት የግብርና ግብዓት በማሰራጨትና ምርትና ምርታማነት በማሳደግ፣



ግርማ አመንቴ (ዶ/ር)

ለግብርና ምርቶች ገበያ በማፈላለግ፣ የሸቀጦችና አገልግሎቶች ዋጋን በማረጋጋት፣ ቁጠባና ኢንቨስትመንት በማስፋፋትና የመኖሪያ ቤቶች ችግር በማቃለል ዘርፈ-ብዙ አገልግሎት በመስጠት ትልቅ አስተዋፅዖ ሲያበረክቱ ቆይተዋል።

በተጨማሪም ለአካባቢያዊ ችግሮች መፍትሔ የሚሆኑ የልማት ሥራዎች ላይም ትኩረት ሰጥተው በመሥራት በመሠረተ ልማት ግንባታ፣ በአረንጓዴ ልማትና በሌሎች ማኅበራዊ ድጋፎች ተሳትፎ በማድረግ ላይ የሚገኙ ተቋማት መሆናቸውም ተናግረዋል።

የኅብረት ሥራ ዘርፍ ትልቅ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያለው ሴክተር ቢሆንም፣ በኢትዮጵያ ያሉ ኅብረት ሥራ ማኅበራት በብዙ ተግዳሮቶች የተከበቡ ተቋማት በመሆናቸው ዘርፉ በሚፈለገው ደረጃ ሊያድግ አልቻለም ሲሉም ገልጸዋል። የሚስተዋለውን የገበያ ግሽበት መቋቋም የሚቻለው እንደ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ያሉ ተቋማትን ተወዳዳሪና ተፅዕኖ ፈጣሪ ማድረግ እንደሚገባም ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ የኅብረት ሥራ ኮሚሽነር ጌታቸው መለሰ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ በአሁን ወቅት በዓለም ላይ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የሌለበት ሀገር ካለመኖሩም በላይ ለበርካታ ሀገራት የኢኮኖሚ ዘርፍ እድገት ትልቅ አበርክቶ ማድረግ የቻሉ ተቋማት መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

እንደ ኮሚሽነሩ ገለጻ፣ በኢትዮጵያ በአብዛኛው የገጠር ቀበሌዎችና በከተሞች ደረጃ ከ28 ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ አባላት ያሏቸው ከ110ሺህ በላይ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበራት፣ 403 ዩኒየኖችና አምስት ፌዴሬሽኖች በግብርና፣ በሸማቾች፣ በቁጠባ፣ በብድር እና በሌሎች ዘርፎች ተደራጅተው እስከ 49 ቢሊዮን ብር ካፒታል ማፍራት ችለዋል።

በማኅበራቱ ከአራት ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል የተፈጠረ ሲሆን፣ የሴቶች የአባልነት ተሳትፎ 33 በመቶ እንዲሁም በአመራርነት 18 በመቶ መድረሱን ኮሚሽነሩ ተናግረዋል።

በገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማኅበራት በተደረገው ጥረት እስከ 50 ቢሊዮን ብር ቁጠባና እጣ በማሰባሰብና በዓመት በአማካይ ከ12 ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ ብድር በማቅረብ ጉልህ አስተዋፅዖ ማበርከታቸውን አንስተዋል።

የኅብረት ሥራ ማኅበራት ለሀገር በቀል ኢኮኖሚ ግንባታ አጋዥ እንደመሆናቸው ለሀገራዊ ለውጥ ዓላማዎች የበለጠ አበርክቶ እንዲኖራቸው የሪፎርም ሥራው ተግባራዊ መደረግ መጀመሩን ገልጸዋል።

# "የኢኮኖሚ እድገቱን ለማፋጠን የዲጂታል ገበያውን ማሳደግ ይገባል"

### - የምጣኔ ሀብትና የፋይናንስ ባለሙያዎች

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡-የኢኮኖሚው ስብራትን ለመጠገንና እድገቱን ለማፋጠን የዲጂታል ገበያውን ማሳደግና የኢንዱስትሪውን አብዮት ማስፋፋት እንደሚገባ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ገለጹ፡፡

የምጣኔ ሀብትና የፋይናንስ ባለሙያው አቶ ኃይለመስቀል ጓዙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ እየተባባሰ የመጣው የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት እንዲያንሠራራ ለማስቻል የዲጂታል ገበያውን ማሳደግ ተገቢ ነው፡፡

ዲጂታል ኢኮኖሚው የፋይናንስ ሥርዓቱን ከማስተካከል በተጨማሪ ዜጎች የያዙትን ገንዘብ በፈለጉት ሰዓት በማንቀሳቀስ ኢንቨስትመንት እንዲጠናከር ዕድል ይፈጥራል ሲሉ አስረድተዋል።

የፋይናንስ ሥርዓቱን ዲጂታላይዝ ማድረግ አንዱ ኢኮኖሚው እንዲያንሠራራ የሚደረግበት መንገድ ነው ያሉት አቶ ኃይለመስቀል፤ የውጭ ባለሀብቶች በዲጂታል ኢኮኖሚው ላይ እንዲሳተፉ መሥራት አስፈላጊ እንደሆነ ጠቁመዋል።

አቶ ኃይለመስቀል አክለውም፤ ማኅበረሰቡ ስለዲጂታል ኢኮኖሚ በተገቢው መንገድ በመገንዘብ ወደ ሥርዓቱ እንዲገባ ምሑራንና የመገናኛ ብዙኃን ኃላፊነታቸው መወጣት እንዳለባቸው ተናግረዋል።

የኢንዱስትሪ አብዮቱ ላይ በሰፊው መሥራት እንዲሁም የሀገር ውስጥ ምርት መጠቀም ያለው አስተዋፅዖ በተመለከተ በዘመቻ መልክ ግንዛቤ መፈጠር እንዳለበትም አቶ ኃይለመስቀል ገልጸው፤ ዲጂታል ኢኮኖሚው የሀገርን አቅም ለማሳደግ አስፈላጊ መሣሪያ መሆኑን አውቆ መተግበር እንደሚገባም አመላክተዋል።

ጥራቱን የጠበቀ የሀገር ውስጥ ምርት በጥራትና በስፋት እየተመረተ ባለመሆኑ በየገበያው የሚገኙት እቃዎች በአብዛኛው ከውጭ ሀገራት የሚገቡ ናቸው፤ ይህ ለኢኮኖሚው ስብራት አሉታዊ ሚና አለው ብለዋል፡፡



ኃይለመስቀል ጓዙ



ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ (ዶ/ር)

በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ኤግዚቢሽን የሚሳተፉ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባለሙያዎችም ኃላፊነት በመውሰድ የውጭ ባለሀብቶችን መሳብና የዲጂታል ኢኮኖሚውን ማሳደግ እንዳለባቸው አቶ ኃይለመስቀል ምክረ ሃሳባቸውን አጋርተዋል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያና የፖሊሲ አማካሪው ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ከውድቀት ለመታደግ የዲጂታል ገበያ አማራጭ ጊዜውን የዋጀ መፍትሔ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

ዓለም ሙሉ በሙሉ ወደ ዲጂታል ኢኮኖሚው እየገባ ነው ያሉት ቆስጠንጢኖስ፤ የሀገሪቱን ዲጂታል ኢኮኖሚው ለማሳደግ የፋይናንስ መሠረታዊ የፖሊሲ ለውጦች ያስፈልጋሉ ብለዋል፡፡

እንደ ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር) ገለጻ፤ የውጭ ባንኮች እንዲገቡ ማበረታታት፣ የካፒታል ገበያ ሥርዓት እውን ማድረግና የኢንተርኔት አገልግሎት ማስፋፋት የዲጂታል ገበያው ለማሳደግ ይረዳል፡፡

ዲጂታል ኢኮኖሚውን የፋይናንስ ብልሹ አሠራሮችን ለመቀነስና ኢንቨስትመንትን ለመሳብ አማራጭ ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል።

ከዲጂታል ፋይናንሱ ጎን ለጎን ኅብረተሰቡ የሀገር ምርት የመጠቀም ፍላጎትን መሠረት ያደረጉ ምርቶች በስፋትና በጥራት ማቅረብ ወሳኝ መሆኑን ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር) አስገንዝበዋል፡፡

በኢኮኖሚው የበለጸጉ ሀገራት ለራሳቸው ሀገር ምርት ቅድሚያ ይሰጣሉ ያሉት ባለሙያው፤ አሁን ያለው ኢኮኖሚ እንዲያንሠራራ ዲጂታል ገበያውን ማጠናከርና በገበያው ላይ መንግሥት ጣልቃ ገብቶ ማስተካከል ይጠበቅበታል ሲሉ ተናግረዋል።

በተጨማሪ ዲጂታል ኢኮኖሚውን ከማሳደግ ባለፈ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የአገልግሎት አሰጣጥ መሻሻልና የአሠራር ሥርዓት ማዘመን ጠቃሚ መሆኑን አመላክተዋል።

# በ2016 በመጀመሪያ አምስት ወራት...



**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ትስስር ሚኒስቴር አስታወቀ።

በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የእንስሳትና እንስሳት ተዋፅዖ የውጭ ንግድ ግብይት ዴስክ ኃላፊ አቶ አበበ ታደሰ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2015 በጀት ዓመት በአምስት ወራት 12 ሺህ እንስሳትን ወደ ውጪ መላክ ተችሏል። በ2016 ዓ.ም በተመሳሳይ ወራት ከ84 ሺህ በላይ እንስሳትን በመላክ ከስድስት ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘት ተችሏል።

የገቢው ማደግ የሚያሳየው በኮንትሮባንድ ይወጡ የነበሩ የቁም እንስሳት ወደ ሕጋዊ እየተመለሱ መሆኑን ነው።

በ2016 ዓ.ም ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር በኮንትሮባንድ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችን የመከላከል ሥራ ተጠናክሮ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ አበበ፤ በየቦታው ያሉ ኬላዎች በኮንትሮባንድ መንገድ ከሀገር ሊወጡ የነበሩ የቁም እንስሳትን ወደ ሀገራቸው የመመለስና እርምጃ የመውሰድ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉም ገልጸዋል።

እንደ ኃላፊው ማብራሪያ፤ ከ2014 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ ማንኛውም የቁም እንስሳት ላኪ ድርጅት የኮንትራት ውል ይገባል። በውሉ መሠረት በተቀመጠው ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ መሠረት ኮንትራት ገብተውና የሚጠየቁትን ሕጋዊ መስፈርቶች አሟልተው ሲገኙ መሸኛ ደብዳቤ ለጉምሩክ ይጻፋል። ይህም እንስሳት በሕጋዊ መልኩ እንዲወጡ ያግዛል።

ከጊዜ ወደ ጊዜ በሕጋዊ መንገድ የሚላኩት እንስሳት ቁጥር መጨመር የቁጥጥር ሥርዓቱ መጠናከሩን ያመለክታል ያሉት ኃላፊው፤ አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያ ካላት የእንስሳት ሀብት አንጻር የተነካ አይደለም። በቀጣይ ቁጥጥር፣ ክትትልና ከዋና መዳረሻ ሀገሮች ጋር ጠንካራ የገበያ ትስስር በመፍጠር ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ የተረጋገጠ የእንስሳት ማቆያ “ኳራንቲን” አልነበራትም ያሉት ኃላፊው፤ ሳዑዲ ዓረቢያና ሌሎች ሀገሮች የቁም እንስሳትን የሚቀበሉት ከተረጋገጠ ኳራንቲን የወጡትን ብቻ ነው። ቀደም ሲል የቁም እንስሳትን ወደ ሳዑዲ ዓረቢያ ለመላክ እንስሳት ጅቡቲ ላይ ኳራንቲን ይገቡ ነበር። ይህን ለማስቀረት በያዝነው ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ የሳዑዲ ባለሀብቶች መጥተው ከሚሌ ኳራንቲን ጥራታቸው የተረጋገጠ 7 ሺህ በጎችን ተቀብለዋል ብለዋል።

በቀጣይም በቀጥታ ወደ ኦማን የሚላክ ይሆናል ያሉት አቶ አበበ፤ በጅግጅጋ፣ በመተማ፣ በሑመራና በሌሎች አካባቢዎች ያሉ የኳራንቲን ጣቢያዎችን በማሟላትና በማጠናቀቅ በቀጥታ ተቀባይ ለሆኑ ሀገራት ጥራቱ የተረጋገጠ የቁም እንስሳትን በተሻለ ዋጋ ለመሸጥ የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን አቶ አበበ ገልጸዋል።

በ2003 ዓ.ም የቁም እንስሳትን በብዛት በመላክ ከ150 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ከዘርፉ ማግኘት ተችሎ ነበር። ይሁንና በ2015 ዓ.ም የወጪ ንግዱ በመጠንና በገቢ በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል።

በዚህም የተነሳ የቀነሰበትን ችግር በጥናት በመለየትና በጥናቱ መሠረት ከሕግ ማዕቀፍ አንጻር መፈታት የሚገባቸውን ችግሮች እንዲፈቱ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ አበበ፤ እንዲሁም ባለድርሻ አካላትን የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ በስፋት እየተሠራ ነው ብለዋል።

# በላሊበላ የተከበረው የገና..

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በተፈጠረው የፀጥታ መደፍረስ የከተማውን የቱሪዝም እንቅስቃሴ አዳክሞት መቆየቱን አስታውሰው፤ ከፌዴራል ጀምሮ፣ በክልልና በከተማ አስተዳደሩ አመራሮች ደረጃ አካባቢው ሠላም መሆኑን በማስተዋወቅ የሀገር ውስጥና የውጭ ቱሪስቶች በዓሉን እንዲታደሙ ማድረግ ተችሏል ሲሉ ጠቁመዋል።

በተሠራው የቅንጅት ሥራ በዓሉን ያለምንም የፀጥታ ችግር በድምቀት መከበሩን አስታውቀው፤ በዓሉ ቱሪዝሙን በማነቃቃት ለከተማዋ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አበርክቷል ብለዋል።

የላሊበላ ከተማ ኢኮኖሚ መሠረቱ የቱሪዝም ዘርፉ ነው ያሉት ኃላፊው፤ በበዓሉ ተሳታፊ ቱሪስቶች አማካኝነት ሆቴሎች፣ ምግብና መጠጥ አቅራቢ ድርጅቶች፣ አስጎብኚዎችና ሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች ተዳክሞ የቆየው ሥራቸው መነቃቃቱ አስረድተዋል።

በበዓሉ ለተገኙት ከ500 ሺህ በላይ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ከ45 በላይ ሆቴሎች አገልግሎት መስጠታቸው አስታውቀዋል።

የበዓሉ ተሳታፊዎች በዓሉን ከማክበር ባለፈ በፀጥታ አካላት አስተባባሪነት የቅዱስ የነአኵቶ ለአብ እና የአሸንተን ማርያም ቤተክርስቲያናትን ጨምሮ በከተማዋ የሚገኙ የተለያዩ ቅርሶችን ተዘዋውረው እንዲጎበኙ መደረጉን ተናግረዋል።

የተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገራት ጎብኚዎች በላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ተገኝተው በዓሉን በማክበራቸው የውጭ ምንዛሪ ገቢው እንዲያድግ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ማበርከቱን ገልጸዋል።

ቀደም ባሉ ዓመታት በነበሩ የገና በዓላት ላይ እስከ ሁለት ሚሊዮን የሚደርሱ ቱሪስቶች እንደሚሳተፉ አስታውሰው፤ በዘንድሮው ዓመት ካለው ወቅታዊ የሠላም ሁኔታ አንጻር 250 ሺህ ቱሪስቶችን ለማስተናገድ ታቅዶ ከ500 ሺህ በላይ ቱሪስቶች መገኘታቸውን አስታውቀዋል።

የላሊበላና የአካባቢው ሕዝብ እንዲሁም የፀጥታ አካላት በአምስቱም የከተማዋ መግቢያ በሮች ቱሪስቶች ገብተው እስከሚወጡ ድረስ አስፈላጊውን ትብብር ማድረጋቸው እንግዳ ተቀባይነታቸውን በተግባር ከማሳየት ባሻገር የአካባቢውን ገጽታ መገንባት አስችሏል ብለዋል።

በአገልግሎቱና በሕዝብ እንግዳ ተቀባይነት የተደሰቱ በርካታ ቱሪስቶች አመስግነው መመለሳቸውን ዲያቆን ተፈራ ተናግረዋል።

የከተማዋን ቱሪዝም አሁን ካለበት ይበልጥ ለማነቃቃት በቀጣይ ለሚከበሩ የጥምቀትና የተለያዩ ሃይማኖታዊና ባሕላዊ በዓላት ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

የደብረ ሮሐ ቅዱስ ላሊበላ ዋና አስተዳዳሪ አባ ሕርያቆስ ፀጋዬ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓልና የቤዛ ኩሉ ሥርዓት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ከተለያዩ ሀገራት የመጡ ምዕመናን በተገኙበት በድምቀት ተከብሯል።

የአካባቢው ምዕመናን በፀሎት በመበርታትና እንግዶችን ተቀብሎ በማስተናገድ ከዋዜማው ጀምሮ በተለያዩ ሃይማኖታዊ ሥነ-ሥርዓቶች በሠላም ማክበር መቻሉን አስታውቀዋል።

# ደብረ ማርቆስ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ከሚያውኩ ተግባራት ራሳቸውን ማቀብ እንዳለባቸው ከወዲሁ ጥሪ አቅርበዋል።

ዩኒቨርሲቲው ወላጆች ወደከተማዋ የሚልኳቸውን ተማሪዎች ተንከባክቦ ለማስተማር ዝግጁ መሆኑንና ለዚህም ከተማሪዎች ኅብረትና ከዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ጋር በመቀናጀት ይሠራል ብለዋል።

ዩኒቨርሲቲው በመመገቢያና በማደሪያ ክፍሎች እንዲሁም በቤተ- መጽሐፍትና በሌሎች አገልግሎት መስጫ ስፍራዎችም ተመሳሳይ ዝግጅት መደረጉን ጠቁመው፤ ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው አስፈላጊው ደህንነትና ጥበቃ እንደሚደረግላቸው ተናግረዋል።

የዩኒቨርሲቲው ሠራተኞች በክልሉ በነበረው የሠላምና ፀጥታ ችግር የተነሳ ተበትነው እንደነበር አስታውሰው፤ አሁን ላይ ወደ ዩኒቨርሲቲው እንዲመጡ ጥሪ ቀርቦ በየዘርፉ ውይይት ተካሂዷል ብለዋል።

የዩኒቨርሲቲው መምህራንና ሠራተኞች ለተማሪዎቹ አገልግሎት በመስጠት ሀገሪቱ የምትፈልገውን ዕውቀት ይዘው እንዲወጡ የሚያስችል ዝግጅት ማድረጋቸውን ገልጸዋል።

ዶክተር ይኸይስ እንዳመለከቱት፤ በክልሉ በሚፈጠረው የፀጥታ ችግርና የመንገድ መዘጋት ለዩኒቨርሲቲው የሚያስፈልገው የምግብና የቁሳቁስ ግብዓት እጥረት እንዳያጋጥም አስፈላጊው ጥረት ይደረጋል።

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በማኅበራዊ የትስስር ገጹ ለ2016 ዓ.ም ለነባርና አዲስ የቅድመ-ምረቃ እና ድረ-ምረቃ ተማሪዎች ጥሪ አድርጓል፡፡

በጥሪው መሠረት የሦስተኛ ዓመት ሁለተኛ ወሰነ




ትምህርትና ከዚያ በላይ ነባር መደበኛ የቅድመ-ምረቃ ተማሪዎች፡- ከጥር 16-17 ቀን 2016 ዓ.ም እንዲሁም የአንደኛና ሁለተኛ ዓመት ነባር ተማሪዎች ከየካቲት 7-8 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ እንዲገቡ ጥሪ ተደርጓል።

በተጨማሪ በ2016 ዓ.ም የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ውጤት ያመጡ አዲስ ገቢ የአንደኛ ዓመት ተማሪዎችና በ2016 በሪሚዲያል ፕሮግራም የተመደቡ አዲስ ገቢ ተማሪዎች ከየካቲት 7-8 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ወደዩኒቨርሲቲው እንደሚገቡ ታውቋል።

በተያያዘ አማራ ክልል የሚገኙ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲና ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የነባርና አዲስ ተማሪዎችን የመመዝገቢያ ጊዜ አስታውቀዋል።

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2016 ዓ.ም አዲስ የተመደቡና የማካካሻ መርሐ ግብር ተማሪዎች እንዲሁም በ2015 ዓ.ም የማካካሻ መርሐ ግብር ወስደው የማለፊያ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ከጥር 21 እስከ ጥር 23 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ እንዲመዘገቡ በማኅበራዊ ትስስር ገጹ ጥሪ አቅርቧል።

በሌላ በኩል ደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲም የ2016 ዓ.ም ነባር መደበኛ ተማሪዎች የምዝገባ ጊዜ ጥር 2 እና ጥር 3 ቀን 2016 ዓ.ም መሆኑን በማኅበራዊ ትስስር ገጹ ይፋ አድርጓል።

# የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ማንጸባረቅ እና የዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴው የወደፊት ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል ማሳየት የሚሉት ጥቂቶቹ መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷን እና የግዛት አንድነትዋን ያስከበረች ጥንታዊት ሀገር እንደመሆኗ ለመላው ጭቁን ሕዝቦች የነፃነት ዓርማ መሆኗን አውስተው፤ “በሊግ ኦፍ ኔሽን” የተወከለች ብቸኛ ነፃ አፍሪካዊት ሀገር ኢትዮጵያ እንደነበረች ተናግረዋል።

እ.ኤ.አ. በ1945 የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መሥራች አባል እንደነበረች አስታውሰው፤ ኢጋድን በማቋቋም እና በመምራት ላይም ኢትዮጵያ ትልቅ ሚና እንዳላት ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ አፍሪካን በመወከል የአየር ንብረት ድርድርን መምራቷን የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ በአምስት ዓመታት ውስጥም ከ32 ነጥብ አምስት ቢሊዮን በላይ ችግኞችን በመትከል ለዓለም አርዓያ እየሆነች እንደሆነ አመልክተዋል፡፡

ኢትዮጵያ ያላት የውጭ ግንኙነት በቀጣናው፣ በአህጉሩ እንዲሁም በዓለም ላይ አዎንታዊ ስሜት የሚፈጥር መሆኑንም ገልጸዋል ።

እንደ አምባሳደር ብርቱካን ገለጻ “ከአፍሪካ መዲናነት እስከ ዓለም መድረክ” በሚል መሪ ቃል የሚደረገው ኤግዚቢሽን ቀደም ሲል እና አሁን ያለውን የኢትዮጵያን ዲፕሎማሲያዊ ጎዞ የሚያሳይ ነው።

ኤግዚቢሽኑ አሳታፊ እና መረጃ ሰጭ መሆኑን ተናግረው የውጭ ጉዳይ ከተመሠረተ ጀምሮ ያሉትን የ116 ዓመታት የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ጉዞ በኤግዚቢሽኑ በብቃት ለማሳየት በቂ ዝግጅት መደረጉን ተናግረዋል።

በኤግዚቢሽኑ ኢትዮጵያ ያለፈችባቸው የዲፕሎማሲ ሥራዎች እና ፈተናዎች በተለያዩ መንገዶች እንደሚቀርቡ ጠቁመው፤ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች እና ምሑራን በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የሚሳተፉበት የፓናል ውይይትም እንደተሰናዳ አመልክተዋል፡፡

ኤግዚቢሽኑ መቀመጫቸውን አዲስ አበባ ላደረጉ የዲፕሎማቲክ እና የዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ አባላት ልዩ ዕድል ይፈጥራል የሚሉት አምባሳደር ብርቱካን፤ የማኅበረሰቡ አባላት ወደ ኢትዮጵያ ሳይንስ ሙዚየም በመምጣት የሀገሪቱን ዲፕሎማሲያዊ ታሪክ እንዲያውቁ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በኤግዚቢሽኑ ማራኪ አቀራረቦች እና የበለፀጉ ይዘቶች መኖራቸውን ጠቁመው፤ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥሪ ወደ ሀገራቸው የመጡ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያንም ኤግዚቢሽኑን በመጎብኘት ስለ አገራቸው እንዲያውቁ እና በአዕምሮአቸው ውስጥ ዘላቂ ትውስታን እንዲያኖሩ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የባሕር በር ዘላቂ የልማት ዋስትና ነው!

ኢትዮጵያ ለዘመናት ስትጠቀምባቸው የቆየቻቸውን የባሕር በሮች ካጣች ወዲህ የባሕር በር ጉዳይ አንገብጋቢ ሆኖባታል። ሀገሪቱ የባሕር በር እጦቱን ወደብ በኪራይ በመጠቀም ለመሻገር ብዙ ሞክራለች። ላለፉት ከሠላሳ ዓመታት በላይም በእዚህ መንገድ ነበር የወጪ ገቢ ሸቀጦችንና ምርቶችን ስታስናግድ የኖረችው።

ለእዚህ የወደብ ኪራይም በየዓመቱ ከአንድ ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር በላይ ስታወጣ መቆየቷን መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህ ወጪ ለሀገሪቱ አዲስ ወጪ ነው። ለተለያዩ ልማታዊና ሰብዓዊ ጉዳዮች ሊታውለው የሚገባትን ይህን ሀብትም ነው ስትገፈግፍ የቆየችው።

ወደብ ከአንድ ሀገር አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት 25 በመቶውን እንደሚሸፍን መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህም በእጅጉ የሚያምና አልምቶ መና እንደመቅረት የሚቆጠር ነው። የወደብ አለመኖር ይህችን ሀገር ምን ያህል እንደጎዳት እነዚህ ሁለት አብነቶች ጥሩ ማሳያዎች ናቸው።

ሀገሪቱ የተያያዘችው የልማት አቅጣጫ የወደብ ፍላጎቷ በየጊዜው እየጨመረ እንዲሄድ የሚጠይቅ ነው። በግብርና፣ በኢንዱስትሪው፣ በማዕድን ዘርፍ የምታካሂዳቸው ሰፋፊ ልማቶች የወደብ ፍላጎቷን በእጅጉ እንደሚጨምሩት ይጠበቃል። ከእነዚህ ዘርፎች የሚገኘውን ምርት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ፣ ዘርፎቹን ለማልማት የሚያስፈልጉትን ማሽነሪዎች፣ ግብዓቶች ወዘተ. ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የባሕር በር በእጅጉ ያስፈልጋል።

ሀገሪቱ እያደገች ስትሄድ፣ የሕዝብ ብዛቷ ሲጨምር የገቢና ወጪ ንግዱም በዚያው ልክ ይጨምራል። በዚህ እንቅስቃሴ የሚወጣውንና የሚገባውን ሸቀጥና ምርት በተሳለጠ መልኩ ማስተናገድ ያስፈልጋል። ፍሰቱ የተሳለጠ መሆን ብቻ አይደለም ያለበት፤ ደኅንነቱም የተጠበቀ ሊሆን የግድ ይላል።

በሌሎች ዘርፎች ለሚካሄዱ ልማቶች የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ለማቅረብ ዋናው መሣሪያ የባሕር በር ነው። ቴሌኮም፣ ትምህርት፣ ጤና፣ ወዘተ ለማስፋፋት፣ የግንባታውን ዘርፍ ለማሳለጥ፣ የትራንስፖርት መሠረተ ልማትን ለማስፋፋት የባሕር በር ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም።

ኢትዮጵያ በልማቱ እያካሄደቻቸው የምትገኛቸውና የምታካሂዳቸው ከትንሽ እስከ ትልቅ ያሉ ልማቶች ያለወደብ ብዙ ርቀት ሊጓዙ አይችሉም፤ አትራፊነታቸውም፣ የዜጎች ተጠቃሚነትም እንዲሁ ያጠራጥራል። አርቆ ለሚያስብ፣ ያለፉትን ፈተናዎች በሚገባ ለተመለከተ መንግሥትና ሕዝብ ደግሞ የባሕር በር ጉዳይ ከምንም በላይ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ተግባሮች አንዱ ነው።

ሀገሪቱ በኪራይ የወደብ አገልግሎት ማግኘትን በሚገባ ሠርታበታለች፤ የጅቡቲ ወደብን በሚገባ በመጠቀምም ልማቷን ስታሳልጥ ቆይታለች። አማራጭ ወደቦችን ለማግኘትም ብዙ ሞክራለች፤ ሶማሊያ በርበራን፣ ፖርት ሱዳንን ፣ የአሰብና የምፅዋ ወደቦችን ለመጠቀም ብዙ ጥራለች። ለሀገሪቱ ሲያገለግል የቆየው የጅቡቲ ወደብ ብቻ ነው። ይህን ሁሉ ስታደርግ የቆየችው ልማቱ እንደሚጠይቃት ስለምትረዳ ነው።

የባሕር በር ጉዳይ በእጅጉ ሲያሳስበው የቆየው መንግሥት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጉዳዩን አጀንዳ አድርጎታል፤ በቅርቡም ጉዳዩ አንገብጋቢ መሆኑን በመጠቀስ ዜጎች የባሕር በር በሰላማዊ መንገድ ማግኘት በሚቻልባቸው መንገዶች ላይ እንዲወያዩ ጥሪ ማቅረቡ ይታወቃል። ይህን ተከትሎም ሕዝቡ ፊትም የባሕር በር አጥብቆ ሲጠይቅ የኖረ እንደመሆኑ የባሕር በር ጉዳይን አጀንዳው አድርጎታል።

መንግሥት በቅርቡ ደግሞ የባሕር በር በሊዝ ማግኘት የሚቻልበትን የመግባቢያ ስምምነት ከሶማሌ ላንድ ጋር ተፈራርሟል። ስምምነቱም ለባሕር በር የሚያስፈልገውን ቦታ በሊዝ ማግኘት የሚያስችል ነው። ስምምነቱ በአጸፋው የሶማሌ ላንድ ከኢትዮጵያ የልማት ድርጅቶች የአንዱ ባለድርሻ እንድትሆን ያስችላታል።

ይህ ሀገሪቱ ዘላቂ በሆነ መልኩ የባሕር በር ባለቤት እንድታገኝ የሚያስችል ውሳኔ ለኢትዮጵያ የብልጽግና ጉዞ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ይዞ እንደሚመጣ ከወዲሁ መናገር ይቻላል። ይዞት የመጣው ዕድል ብዙ ነው። የሀገሪቱን ዕድገት ዘላቂ ማድረግ ያስችላል፤ ሀገርን ከወደብ ኪራይ ይታደጋል፣ ሀገሪቱ ባሕር ላይ የምትንቀሳቀስበትን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ለደህንነትም ዋስትና ይሆናል። በአካባቢው ካሉ ሀገሮች ጋር አብሮ መልማት እንደሚቻልም ማሳያ ሊሆን ይችላል።

የሀገሪቱ የባሕር በር በሊዝ የመያዝ ስምምነት በዓለም አቀፍ ደረጃም ይሠራበታል። የተለያዩ ሀገሮች የባሕር በር በሊዝ ይዘው እየሠሩ ይገኛሉ። ኢትዮጵያም ያደረገችው ይህንኑ ነው። መንግሥት ይህን ዓለም አቀፍ ተሞክሮ አምጥቶ ለሀገር የሚበጅ ዘላቂ የወደብ አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችል ውሳኔ ላይ መድረሱ በወሳኝ ወቅት የተወሰደ ትክክለኛ ርምጃ ነው።

120 ሚሊዮን ሕዝብ ይዞ በአንድ ወደብ ላይ ተረጋግቶ መኖር ይከብዳል፤ ለዚያውም በኪራይ። በግብርናው በኢንዱስትሪውና በማዕድን ዘርፍ የሚደረጉ ልማቶች የሚያስገኙትን ውጤት እንደልብ ማውጣት፣ ለብልጽግና ጉዞ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት የሚያስችል የባሕር በር በሌለበት ሁኔታ ልማቱን ዘላቂ ማድረግም ፈታኝ ይሆናል።

የባሕር በር አለመኖር የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ሊገፋ እንደሚችል ጥርጥር የለውም። ይሄ ደግሞ ዓለም የሚሻማበትን የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መግፋት ይሆናል። ኢንቨስተሮች የባሕር በር፣ የሸቀጣቸው ደህንነት እንዲጠበቅና ርካሽ የማጓጓዣ አገልግሎት ይፈልጋሉ፤ ርካሹ የማጓጓዣ ትራንስፖርት ከሆነው የባሕር ትራንስፖርት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ያደርጋል። የባሕር በር መኖሩ እነዚህን ችግሮች ሁሉ ይፈታል።

የምጣኔ ሀብቱን እድገት የሕዝብ ብዛቱን እየጨመረ መምጣት ተከትሎ የሚፈጠሩ ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ልማቶችና አገልግሎቶችን ለማድረስም ዘላቂ የባሕር በር መኖሩ የግድ ነው። ለዚህ ደግሞ መንግሥት ከሶማሌ ላንድ ጋር የደረሰበት ስምምነት ፋይዳ ከፍተኛና ለዘላቂ ልማትም ዋስትና ነው!


**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ከሀብት መመዝበሪያነት፤ ወደ ሀብት ማፍሪያነት

ዘካርያስ

ለሀገር ልማት የሚበጁ ፕሮጀክቶችን ለመገንባት የመንግሥትና የሕዝብ ቁርጠኝነት፣ የተፈጥሮና የመሳሰሉት ሀብቶች፣ የተማረ የሰው ኃይል፣ ገንዘብ፣ በዋናነት አስፈላጊ በመሆን ሊጠቀሱ ይችላሉ። እነዚህ የልማት ግብዓቶች አንዱ ለአንዱ ወሳኝ ቢሆኑም፣ ሁሉንም ግን ያለ ገንዘብ ማሰብ ይከብዳል።

የቱንም ያህል የተፈጥሮ ሀብት ቢኖር፣ ያለ በቂ ገንዘብ ልማት ውስጥ ዘሎ አይገባም። የቱንም ያህል የተማረ የሰው ኃይል ቢኖር፣ የቱንም ያህል የሕዝብና መንግሥት ቁርጠኝነት ቢኖር ያለ ገንዘብ ሊታሰብ የሚችል ልማት አይኖርም። የመልማት ፍላጎትና የማልማት አቅም እየተጤነ ወደ ልማት የሚገባውም ለእዚህ ነው።

ኢትዮጵያም ከሀገር ውስጥ ከተለያዩ ምንጮች መሰብሰብ በምትችለው ሀብት፣ ከዓለም አቀፍ ተቋማትና ካደጉት ወዳጅ ሀገሮች ልታገኛቸው በምትችላቸው ብድርና እርዳታዎች እንዲሁም ሕዝቧን አስተባብራ ልታገኝ በምትችለው ሀብት ልክ ነው ማልማት ውስጥ ስትገባ የቆየችው። እነዚህ የልማቱ ምቹ እድሎች ተደርገው ሲወሰዱ ቆይተዋል። በልማቱ ምቹ ሁኔታዎቹ ብቻ አይደለም ታሳቢ ተደርገው ሲታዩ የነበሩት፣ ስጋቶችና መፍትሔዎቻቸውም ጭምር ናቸው።

ሀገሪቱ የበርካታ እምቅ ሀብቶች ባለጸጋ ናት። በግብርናው፣ በቱሪዝሙ፣ በማዕድኑ፣ በውሃ ሀብቱ ወዘተ እምቅ ሀብት ሞልቷታል። ይህ ሀብት በእምቅ ሀብትነት መኖሩ ምቹ ሁኔታ ከሚባሉት መካከል ሊጠቀስ ይችላል። ሀብቱ ብቻውን ግን የልማት ፋይናንስ ሲሆን አልተመለከትንም፤ በኛ ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ ለማለት ነው። የከብት ሀብታችንን እየቆጠርን፣ የውሃ ሀብታችንን እየጠቀስን፣ ምቹ የአየር ንብረትና ለም አፈር ያለን መሆኑን እየጠቀስን ከመኖር የዘለለ ያፈራነው ሀብት ብዙም አለመኖሩም ይህንኑ ያመለክታል።

እርግጥ ነው እነዚህ የተፈጥሮ ሀብቶች ለልማቱ ዋስትና ሊሆኑ ይችላሉ። በአንዳንድ ሀገሮች እንደ ነዳጅ ያሉት የተፈጥሮ ሀብቶችን የውጭ ኩባንያዎች የሚያለሙት ይህ ሀብት ሲወጣ ለተወሰኑ ዓመታት አብዛኛውን እጅ ለመውሰድ የሚያስችላቸውን ስምምነት እያደረጉ ነው ይባላል።

ይህ ሁኔታ በሀገራችን መሬት ያላቸው የእኩል እንደሚያሳርሱት አይነት ማለት ሊሆን ይችላል። ድርጅትን እንደ ማከራየት አይነት ማለትም ሊሆን ይችላል። ወደፊት የሚሆነውን ባላውቅም፣ እኛ በውጭ ኩባንያዎች እንደ ነዳጅ ያሉ ተፈጥሮ ሀብቶችን በሆነ እጅ ለተወሰነ ጊዜ ለማልማት የሰጠነው ኩባንያ ያለ አይመስለኝም።

የተፈጥሮ ሀብቶቻችንንም ሆነ ሌሎች ሀብቶቻችንን ላለማልማታችን ምክንያቶቹ ብዙ ሊሆኑ ቢችሉም፣ አንዱ ምክንያት ሆኖ የሚጠቀሰው በቂ ገንዘብ አለመኖር ነው። እነዚህን የተፈጥሮና የመሳሰሉትን ሀብቶች ለማልማት እርሾ በመሆን የሚያገለግል በቂ ገንዘብ ያስፈልጋል። ከዚህ በሚገኘው ገንዘብ አንዱን ባንዱ እንዲሉ ደግሞ ሌላውን ማልማት ይቻላል። በመሆኑም ለእኛ ሀገር ልማት ገንዘብ ወሳኙ ግብዓት ነው።

ይህን ሀብት ማግኘት ላይ ሀገሪቱ ብዙ ጥረት አድርጋለች፤ እያደረገችም ትገኛለች። በግብር መሰብሰቡ፣ ከውጭ ብድርና እርዳታ በማፈላለጉ፣ ዜጎች በልማቱ በስፋት እንዲሠማሩ በማድረጉ ላይ ሠርታለች። በዚህም ለውጦች እንዳሉ ይታወቃል፤ የዓባይ ግድብን ያህል በዓለምም በአፍሪካም ተጠቃሽ ፕሮጀክት ማልማት የተቻለው በሕዝብና በመንግሥት ሀብት መሆኑ ለእዚህ አንድ ሁነኛ ማሳያ ነው።

እንደ ሀገር ያለው የልማት ፍላጎት ከፍተኛ ቢሆንም፣ ለእዚህ የሚሆነው ሀብት ውስን በመሆኑ ሳቢያ የተወሰነውን ጥያቄ ለመመለስ ሲሠራ ቆይቷል። ለእዚህ ምክንያቶቹ ለልማትና ለመሳሰሉት ሊውል የሚችለው ሀብት ማግኛ ከሆኑት መንገዶች መካከል አንዱ የሆነው የግብር አሰባሰብ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ደካማ የሚባል ነበር። ኢኮኖሚው የሚያመነጨው ገቢ እየተሰበሰበ ስላለመሆኑ መንግሥትም የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎችም ሲያሳስቡ ቆይተዋል።

> በተደጋጋሚ መመልከት እንደተቻለው፤ ከለውጡ ወዲህ መንግሥት የያዛቸው ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እየተጠናቀቁ ይገኛሉ። የዓባይ ግድብም ከዚያ የውድቀት አፋፍ ወጥቶ መብራት መሆን መጀመሩ፤ የኢንዱስትሪዎችን የኃይል ፍላጎት ጥያቄ ለመመለስም እያገዘ መሆኑ ለእዚህ በአብነት ሊጠቀስ ይችላል

ለውጭ ገበያ የሚቀርቡት አብዛኛዎቹ ሸቀጦቻችን ዛሬም የግብርና ምርቶች ናቸው። እርግጥ ነው እንደ ወርቅ ያሉት ማዕድናት ለውጭ ገበያ ሲቀርቡ ኖረዋል፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ አልባሳትና የኤሌክትሪክ ኃይል ለውጭ ገበያ እየቀረቡ ናቸው። ከእነዚህ የሚገኘው ሀብት ብዙ ሊያግዝ ቢችልም፣ በቂ የሚባል ግን አይደለም።

የውጭ ብድርና ርዳታ ሌላው የልማቱ ፋይናንስ ነው። በእነዚህም መንገዶች፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ የኃይል ማምንጫዎች ተገንብተዋል። ይህን ብድርና ርዳታ የሚዘውሩ ሀገሮችና ተቋማት በሚፈጥሩት ጫና ብድርና ርዳታው በሚፈለገው ልክና ጊዜ ለሀገሪቱ የማይደርስበት ሁኔታ እንደመኖሩ፣ አስተማማኝ የልማት አቅም ተደርጎ ሊያዝ አይችልም።

በሰሜን ኢትዮጵያው ጦርነት ወቅት እነዚህ ኃይሎች በኢትዮጵያ ላይ በፈጠሩት ጫና ኢትዮጵያ

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

## ከሀብት መመዝበሪያነት፣ ወደ. . .

ከ ገጽ 5 የዞረ

እነዚህን ጥቅሞች እንዳታገኝ መደረጓ ይታወቃል። በእዚህ ዓይነቱ ሁኔታ የቅርብ ጊዜው ከፋ እንጂ አበዳሪ እና ለጋሽ ተቋማትና ሀገሮች በሀገሪቱ ላይ በሚፈጥሩት ጫናዎች የተነሳ በውጭ ብድርና እርዳታ ግኝት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ሲያሳርፉ ቆይተዋል።

በብዙ ፈተና የሚገኘውን ሀብት ታሳቢ በማድረግ ሀገሪቱ የአስርና የአምስት ዓመት የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ አዘጋጅታ በርካታ ፕሮጀክቶች ቀርጻ ወደ ትግበራ ገብታ እንደነበርም ይታወቃል። የታየው ለውጥ ግን ብዙም አልሆነም። ከተወሰኑት በስተቀር አብዛኛዎቹ መክነዋል፤ ቆመው ቀርተዋል። ለምን ብሎ መጠየቅ ጥሩ ነው።

ያ ዘመን በሀገራችን ከፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ ብዙ ድክመት የታየበት ዘመን ነበር፤ የዚያ ዘመን የፕሮጀክቶች በሽታ በርካታ ፕሮጀክቶች እንዳይሆኑ አርጓል። የሀገሪቱን የስኳር ችግር ይቀርፋሉ ተብለው በርካታ የስኳር ፕሮጀክቶች ተጀምረው እንደነበር ይታወሳል። የሀገር ውስጥ ፍጆታን ከመሸፈን አልፈው ስኳር ለውጭ ገበያ የሚቀርብበት ሁኔታ እንደሚፈጠር ብዙ የተባለላቸው ቢሆንም፣ ዛሬ እጃችን ላይ የገባ ነገር የለም።

ፕሮጀክቶቹ የሀገር ውስጥ የስኳር ፍጆታን ሊመለሱና ለውጭ ገበያ ስኳር ሊያቀርቡ ቀርቶ ራሳቸውን የማያድኑ የእንጨት ምንቸት ሆነው ቀርተዋል። የዚህች ድሃ ሀገርና ሕዝብ ሀብት የተንዳሆ ስኳር ልማትን በሚል አሸዋ ውስጥ ቀርቷል፤ ግንባታቸው ተጠናቆ ወደ ሥራ ገቡ ከተባሉት የስኳር ፕሮጀክቶች ስኳር ብልጭ ብሎ ድርግም ከማለቱ ውጪ የታየ የሀገር ችግር የሚፈታ ምርት አልታየም። እየተሰማ ያለው ሀገሪቱ ስኳር ከውጪ እያስገባች መሆኑ ነው።

በያዩ የማዳበሪያ ፋብሪካ ለመገንባት በሚል ስም የሀገር ሀብት መቀመቅ ገብቷል። አሁንም ድረስ የሚጨናበሱ የመስኖ ፕሮጀክቶች እንዳሉ ይታወቃል። የዚያ ዘመኑ ዘረፋ ዜኀች ከአፋቸው ክፍለው ለዓባይ ግድብ ግንባታ ያዋጡትንም አልማረም። ከፕሮጀክቶቹ ፍሬውን ማጣጣም የተቻለው በኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨቱ በኩል በተያዙ ፕሮጀክቶች ናቸው።

እነሱም ውጤታማ መሆን የቻሉት በለውጡ መንግሥት ቁርጠኛ አመራር ነው። የዓባይ ግድብ ግንባታ የለውጡ መንግሥት ባይደርስለት ኖሮ እጣ ፈንታው ከፍ ብለን ከጠቀስናቸው ፕሮጀክቶች መካከል ሊሆን እንደሚችል ጥርጥር የለውም። የለውጡ መንግሥት ለእዚህ ፕሮጀክት በነፍስ ደርሶለትና እስትንፋስ ዘርቶበት ዛሬ ለደረሰበት ታላቅ ምዕራፍ አብቅቶታል።

የእዚያ ዘመን የግንባታ መጓተት ችግር ሀገሪቱን ግንባታ የሚጓተትባት ሀገር አርጓት ቀርቷል። ችግሩ ቀደም ባሉት ዓመታት በተነቃቃ ሁኔታ ውስጥ የነበረውን የግንባታውን ኢንዱስትሪ ስም ጭምር ሰብሮታል። ትላልቅ የግንባታ ፕሮጀክቶች ያሏቸው ተቋማት /መንግሥትን ጨምሮ/ በሀገሪቱ የግንባታ ተቋራጮች ላይ እምነት እንዳያድርባቸው አርጓል።

በሌለው አቅም አለው ተብሎ በተቋራጭነት እንዲኮፈስ የተደረገው ሜቴክ መሪዎችና ፕሮጀክቶቹን በባለቤትነት ፣ በተቆጣጣሪነት ወዘተ ሲመሩ የነበሩ አካላትና የጥቅም ተጋሪዎቻቸው በታቀደ አግባብ የፕሮጀክቶቹን ሀብት ፈንጭተውበታል። ሜቴክ ሀገሪቱን እዳ አስታቅፎ ቢጠፋም መሪዎቹ በአንድም ይሁን በሌላ ሀብት አካብተውበታል። በዚህ የተነሳ ፕሮጀክቶቹ አንድ እርምጃ ሳይጓዙ የተመደበው በጀት እያለቀ ተጨማሪ በጀት ሲጠየቅባቸው ኖረዋል።

በፕሮጀክቶች ላይ የተፈጸመው ጥፋት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ንቃቃት እስከ መሆን ደርሷል። በንቃቃቱ ውስጥ ጥቂት የማይባሉ የውጭ የግንባታ ተቋራጮች የገቡበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ኩባንያዎቹ ለምን ወደ ሀገሪቱ መጡ አላልኩም፤ መግባት ያለባቸው የኛዎቹ አቅም በማጣታቸው ሳቢያ ሲሆን ግን ያማል። የውጭ ኩባንያዎች መምጣትን በሚገባ መጠቀም ከተቻለ ለእውቀትና ለቴክኖሎጂ ሽግግር ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ስለመሆኑ የመንግሥትም

**ፕሮጀክቶቹ ዘመናዊ፣ የከተማዋን ገጽታ በእጅጉ ሊገነቡ የሚችሉ፣ በግንባታ ወቅትና አገልግሎት መስጠት ሲጀምሩ ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር ያስቻሉም ናቸው**

እምነት ነው፤ የኮንስትራክሽን ዘርፉ ተዋንያንም እምነት እንደሚሆን አስባለሁ።

በፕሮጀክቶች ላይ የደረሰው ስብራት ጥሎት ያለፈው ጠባሳ የግንባታ ኢንዱስትሪውን ክፉኛ ጎድቶታል፤ የሀገሪቱ የግንባታ ተቋራጮች መንግሥት ግዙፍ ፕሮጀክቶች ሲያስብ ላወዳድራቸው ቢል እንኳ ተወዳድረው የሚያልፉ አይነት አይደሉም እየተባሉ ነው። በኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ላይ ያ ሁሉ ችግር የተፈጠረው ለፕሮጀክቶች የተመደበውን ሀብት ለመቀራመት የተሠማሩ አካላት በፈጸሙት ሙስና ነው።

ሀገሪቱ ለፕሮጀክቶቹ የሚያስፈልገውን ሀብት መድባ ወደ ትግበራ ገብታ ባለችበት ሁኔታ ፕሮጀክቶች ችግር ውስጥ የገቡት ለፕሮጀክቶች በሚያስፈልግ የሀብት እጦት ሳይሆን በሀብት መዝባሪዎች ሳቢያ ነው። ሀገሪቱ ምንም እንኳ ለልማት የምታውለው በቂ ሀብት ሳይኖራት፣ የልማቱን አስፈላጊነት ግምት ውስጥ በማስገባት ከዚህም ከዚያም ብላ የመደበችው ሀብት ነው ለእዚህ የተዳረገው። ፕሮጀክቶቹ እንዳይጠናቀቁ ያደረገው የሀብት አለመመደብ ሳይሆን የገንዘብ ቀበኞቹ በመክፋታቸው ነው።

በአንጻሩ ከለውጡ ወዲህ የሚገነቡ በርካታ የመንግሥት ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ሲጠናቀቁና ወደ አገልግሎት ሲሸጋገሩ እየተመለከትን ነው። ይህ ብቻ አይደለም አንዳንድ ከለውጡ በፊት የተጀመሩና ሲጓተቱ የቆዩ ፕሮጀክቶችም የዚህ እድል ተቋዳሽ እንዲሆኑ ተደርገዋል።

ይህን መመልከት በራሱ አንድ ለውጥ ነው። መንግሥት ግንባታቸው የተጓተተ እንደ ዓባይ ግድብ ያሉትን ፕሮጀክቶች ችግር በማጥናትና መፍትሔ በማስቀመጥ ያከናወናቸው ተግባሮች እንዲሁም በራሱ አቅዶ በመጀመር ያጠናቀቃቸውና እያጠናቀቃቸው የሚገኙ ፕሮጀክቶች ፕሮጀክትን በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ ማጠናቀቅ እንደሚቻል ማሳያ ተደርገው ብቻ የሚወሰዱ አይደሉም፤ ለግንባታ መጓተት ምክንያት ከሆኑት መካከል የሚጠቀሰውና ይህን ተከትሎ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ለገባው የግንባታው ኢንዱስትሪ እስትንፋስ እፍ የተባለባቸው ናቸው ማለትም ያሰኛል።

በተደጋጋሚ መመልከት እንደተቻለው፤ ከለውጡ ወዲህ መንግሥት የያዛቸው ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እየተጠናቀቁ ይገኛሉ። የዓባይ ግድብም ከዚያ የውድቀት አፋፍ ወጥቶ መብራት መሆን መጀመሩ፤ የኢንዱስትሪዎችን የኃይል ፍላጎት ጥያቄ ለመመለስም እያገዘ መሆኑ ለእዚህ በአብነት ሊጠቀስ ይችላል። አምና ኃይል ወደ ማመንጨት ከተሸጋገሩት ሁለት የኃይል ማመንጫዎች በተጨማሪ አምስት ማመንጫዎች ዘንድሮ ወደ ሥራ እንደሚገቡ ይጠበቃል። ይህ ሁሉ የሆነው የለውጡ መንግሥት ፕሮጀክቱን ከወድቀት ለመታደግ ባደረገው ርብርብ ነው።

በጠቅላይ ሚኒስትሩ አስተባባሪነት ተገንብተው ወደ ሥራ ከገቡ ዓመታት ያስቆጠሩት የገበታ ለሸገሮቹ አንድነት፣ ወዳጅነት እንዲሁም እንጦጦ ፓርኮች በምን አይነት ፍጥነት ተገንብተው ወደ ሥራ እንደገቡና ለቱሪዝሙ ዘርፍ መነቃቃት ጉልህ አስተዋፅዖ እያበረከቱ መሆናቸው ይታወቃል።

በገበታ ለሀገር ከተጀመሩ ፕሮጀክቶች የኮይሻ ፕሮጀክት አካል የሆነው በዳውሮ ዞን የተገነባው የሀላላ ኬላ ሪዞርት ተመርቆ ወደ ሥራ ገብቷል፤ በቅርቡ ደግሞ የዚሁ የኮይሻ ፕሮጀክት አካል የሆነው የዳና ሎጅ ግንባታ ተጠናቆ ተመርቋል። የወንጪ ደንዲ የኤኮ ቱሪዝም ፕሮጀክትም እንዲሁ በቅርቡ እንደሚመረቅ ይጠበቃል። የጎርጎራ ፕሮጀክትም ግንባታው እየተካሄደ ይገኛል። ሌሎች በርካታ ተመሳሳይ ስምንት ፕሮጀክቶችን በገበታ ለትውልድ ፕሮጀክት በተለያዩ ክልሎች ለመገንባት ታቅዶ የአንዳንዶቹም ሥራ ተጀምሯል።

በአዲስ አበባ ከተማም በርካታ የመንገድ ፕሮጀክቶች ግንባታ ተጠናቆ ወደ ሥራ እንዲገቡ ተደርጓል፤ የሳር ቤት ጎፋ ማዞሪያ ጎተራ መንገድ ለእዚህ በአብነት ይጠቀሳል። የቃሊቲ ቱሉ ዲምቱ የመንገድ ፕሮጀክት ከፋይናንስ አቅራቢው የውጭ ድርጅት ጋር ፋይናንስ አለማቅረብ ጋር በተያያዘ መጓተት ታይቶበት ቢቆይም፣ የከተማ አስተዳደሩ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት የመንገዱን ግንባታ ወደ ማጠናቀቂያ ምዕራፍ ማድረስ ተችሏል። የመንገዱ ግንባታ እስኪጠናቀቅ ድረስ ሳይጠበቅ አገልግሎት እንዲሰጥም ነው የተደረገው፤ በሌሎች ፕሮጀክቶች ላይም እንዲሁ በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት መጠናቀቅ ብቻ ሳይሆን በፍጥነት አገልግሎት እንዲጀምሩ ሲደረጉም እየተመለከትን ነው።

የመስቀል አደባባይ፣ የአብርኆት ቤተመጽሐፍት፣ የሳይንስ ሙዚየም፣ የአንድነት ፓርክ የተሽከርካሪ ማቆሚያ፣ የግብርና ምርቶች ግብይት ማዕከላትና የመሳሰሉትና ሌሎች ግንባታቸው እየተካሄደ የሚገኝ በርካታ ፕሮጀክቶችም እንዲሁ ከዚሁ አኳያ የሚታዩ ናቸው። ፕሮጀክቶቹ ዘመናዊ፣ የከተማዋን ገጽታ በእጅጉ ሊገነቡ የሚችሉ፣ በግንባታ ወቅትና አገልግሎት መስጠት ሲጀምሩ ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር ያስቻሉም ናቸው። በመሬት አጠቃቀም በኩልም እንዲሁ በምድር ውስጥ በርካታ ተሽከርካሪዎችን ማቆም የሚችሉ ግንባታዎች ናቸው።

የእነዚህ ፕሮጀክቶች ግንባታ በተያዘለት ጊዜ መጠናቀቅ ግንባታ ሲጓተትባት ለቆየችው ኢትዮጵያ ግንባታ ተጀምሮ ሊጠናቀቅ እንደሚችል ጥሩ ማሳያዎች ናቸው። ግንባታ ፈጥኖ ተጠናቀቀ ማለት በግንባታ መጓተት ሳቢያ ተጨማሪ ሀብት እየተጠየቀባቸው ከፍተኛ በጀት የሚያስወጡ ፕሮጀክቶች እንዳይፈጠሩ ማድረግ ይቻላል ማለት ነው።

ከለውጡ ወዲህ ወደ ግንባታ ገብተው በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ትምህርት ለሚቀስማባቸው ጥሩ ትምህርት ቤቶች መሆን የሚችሉ ናቸው። በተለይ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ተዋንያን ይህን ትምህርት ቤት መቀላቀልና ዘርፉን ለመለወጥ መሥራት ይኖርባቸዋል። ከእነዚህ ግንባታዎች አንዳንዶቹ በሀገር ውስጥ ተመራጮች አንዳንዶቹ በውጭ ተቋራጮች ነው የተገነቡት። የተገነቡት ግን እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ ነው።

የግንባታው ዓውድ ያለው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ ብሎ መጠየቅና የራስን አሰላለፍ ማስተካከል ከኮንስትራክሽን ዘርፉ ተዋንያን ይጠበቃል። ለእዚህ ደግሞ ጥናት ማድረግ፣ አቅማቸው የት ቦታ ላይ እንደሆነ መለየት፣ ከለውጡ ወዲህ ግንባታቸው የተጠናቀቀና ወደ ሥራ የገቡ እንዲሁም ግንባታቸው ተጠናቆ ወደ ሥራ ለመግባት የተቃረቡ ፕሮጀክቶች ተቋራጮችን አሠራር መቃኘት ይኖርባችኋል።

እስከ ለውጡ ድረስ ፕሮጀክቶች የሙሰኞች የሀብት ምንጭ ሆነው ቆይተዋል። የእነዚህ ሁሉ ፕሮጀክቶች ሀብት በተለያየ ደረጃ ባሉ ሙሰኞች ተዘርፏል። ፕሮጀክት ሲታሰብ መንግሥትና ሕዝብ የሚጠብቃቸው ስለመሆናቸው ሳይሆን፣ በፕሮጀክቶቹ ዙሪያ ያሉ ሌቦች ሀብታቸውን የሚቀራመቷቸው ተደርገው ሲታዩ ቆይተዋል።

ሀገሪቱ የቱንም ያህል ውስን ሀብት ቢኖራት፣ ለልማት ፕሮጀክቶቿ ትኩረት በመስጠት ሀብት ስትመድብ ኖራለች፤ ችግር ሆኖ የነበረው ይህን ሀብት በአግባቡ አለመጠቀም ላይ ነው። አሁን ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ይህን ለመለወጥ እየሠራ ነው፤ ለውጦችንም እያሳየ ይገኛል።

አሁን ነገሮች ተቀይረዋል። ፕሮጀክቶች የሙሰኞች የሥርግና ምላሽ መፈንጠዣዎች ሳይሆኑ የመንግሥትና ሕዝብ ጥያቄ መመለሻዎች መሆን ጀምረዋል። ይህ ሊሆን የቻለው ደግሞ ለፕሮጀክቶች የተመደበውን ሀብት በሚገባ ሥራ ላይ በመዋል ነው። ሌላው ለፕሮጀክቶች በጊዜ መጠናቀቅ ምክንያት ተብሎ መያዝ ያለበት የፕሮጀክቶች ባለቤቶች ፕሮጀክቶችን ነጋ ጠባ እየጎበኙ አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረጉ ያለበት ሁኔታ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድና(ዶ/ር) ከንቲባ አዳነች አቤቤ ፕሮጀክቶችን በመጎብኘትና በመከታተል ሊጠቀሱ የሚገባቸው ናቸው።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ባለዘርፈ ብዙ አገልግሎት ሮቦት ፈጣሪው ተማሪ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ተማሪ በንያስ ወንደወሰን ይባላል። የ12ኛ ክፍል ተማሪ ሲሆን በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ታለንት ማዕከል ከታቀፉ ባለተሰጥኦዎች አንዱ ነው። ተማሪ በንያስ በማዕከሉ የተለያዩ የፈጠራ ሥራዎች በመስራት ያለውን የፈጠራ ችሎታና ተሰጥኦውን እያሳየ ይገኛል። ቀደም ሲል ሁለት የፈጠራ ስራዎች ያሉት ተማሪው፣ በአሁኑ ወቅትም ቤት ውስጥ በረዳትነት የምታገለግልና የደህንነት ሥራ የምትሰራ ሮቦት ሰርቷል።

ተማሪ በንያስ ይህን የፈጠራ ሥራ ለመስራት መነሻ የሆኑት በአካባቢው የሚያያቸው ነገሮች ናቸው። በየቤቱ ከሚያየው ችግር ተነስቶ ሰውን ተክቶ በቤት ውስጥ በረዳትነት ሊያገለግል የሚችል ነገር መኖር እንዳለበት ያስባል። ይህን መስራት የሚያስችለውን አጋጣሚ አገኘናም ሀሳቡን ወደ ተግባር ቀየረው። በየአካባቢው ከሌባ ጋር ተያይዞ ከሚነሱ ስጋቶች ጀምሮ ሌሎች የአደጋ ስጋቶች በመነሳትም በደህንነት ላይ ትኩረት አድርጎ ሰርቷል።

በርካታ የፈጠራ ሀሳቦች በውስጡ ይዞ የሳይበር ታለንት ማዕከልን መቀላቀሉን የሚናገረው ተማሪ በንያስ፣ ማዕከሉ መግባቱ ከሳይበር ደህንነት ጋር በተያያዘ የሚያስበውን ሁሉ አጠናክሮ እንዲቀጥል እንዳደረገው ይናገራል። ቀደም ሲልም ሁለት የሮቦት ፈጠራ ሥራዎች ሠርቶ እንደነበር አስታወሶ፣ ይህ ሮቦት ሦስተኛው የፈጠራ ስራው መሆኑን ይናገራል። የፈጠራ ሥራውን በማዕከሉ ጀምሮ እያሳደገ አሁን ያለበት ደረጃ እንደ ደረሰም ይገልጻል።

ተማሪው የፈጠራ ሥራውን ገና ከልጅነቱ ጀምሮ ይሞክር፣ አገልግሎት ላይ ከማይውሉ እና ከወዳደቁ ነገሮች የፈጠራ ሥራዎች በመስራት በቅርቡ ላሉ ሰዎች ያሳያቸውም ነበር። ለፈጠራ ሥራዎች የተለየ ፍቅር ስለነበረው በትምህርት ቤቱ ያለውን እምቅ የፈጠራ ችሎታ በማሳየት ከማይጠበቁ ነገሮች የሚፈጥራቸውን የፈጠራ ሥራዎች ለመምህሮቹና ለትምህርት ቤት ጓደኞቹ ያሳይ እንደነበርም ያስታውሳል። ይህን የተመለከቱ መምህራኖቹና የትምህርት ቤት ጓደኞቹ ሞራል በመስጠት አበረታትውታል።

ሳይበር ታለንት ማዕከልን ከተቀላቀለ በኋላ ደግሞ በተሰጠው ስልጠናና ሙያዊ እገዛ የተነሳ ከፍ ያለ ሥራ መስራት እንደቻለ የሚገልጸው ተማሪ በንያስ፣ በዚህም በአንድ ጊዜ ዘርፈ ብዙ አገልግሎት መስጠት የምትችል ሮቦት መስራቱን ይገልጻል። ሮቦቷን የቤት ውስጥ ረዳትነት አገልግሎት እንድትሰጥና የደህንነት ሥራዎችን እንድትሰራ በማሰብ መስራቱን ጠቅሶ፣ ሮቦቷን ለመስራት ከተጠቀመባቸው ቁሳቁስ አንዳንዶቹ አገልግሎት ያቆሙ መሆናቸውን ይጠቁማል።

ተማሪ በንያስ እንዳብራራው፣ ሮቦቷ አይኗ አካባቢ የፊት ገጽን ፎቶ የሚያነሳ ቁስ ተገጥሞላታል፤ በዚህም እንደ ፈለገች እየተሽከረከረች የአካባቢውን ፎቶ በማንሳት ደህንነት የመጠበቅ ስራዋን ትሰራለች። ከዚህም በተጨማሪም ቤት ውስጥ ምን እየተካሄደ እንደሆነ፣ በተለይም ሌባ ቢገባ ወይም ሌላ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ክስተት ቢፈጠር የሌባውን ወይም የክስተቱን እንቅስቃሴ በመመዝገብ በየአንድ ሰዓቱ ልዩነት ለሚቆጣጠራት አካል ሪፖርት ታደርጋለች፤ መልዕክቶችንም ትልካለች።

ሮቦቷ ሌሎች በርካታ ጥቅሞች እንዳላትም ተማሪ በንያስ ይገልፃል። ከሰዎች ጋር በአማርኛ ቋንቋ መግባባት ትችላለች። ሰዎች የሚያሰሙትን ድምጽ መልሳ ታሰማለች፤ ለሚቀርብላት ጥያቄ ምላሽ ትሰጣለች። ለምሳሌ ‘ሰላም’ ተብላ ሰላምታ ስትጠየቅ ‘ሰላም’ በማለት አጸፋውን እንደምትምልስ ነው ያስረዳው። በተጨማሪም ሮቦቷ ደህንነታቸው እንዲጠበቅ የሚፈለጉ ነገሮች ደህንነት እንዲትጠብቅ የተሰጣትን ኃላፊነት እንደምትወጣ ይናገራል።

ተማሪ በንያስ እንደሚለው፣ ሮቦቷ የሬዲዮ ሞገድ ደህንነት በመጠበቅ ረገድ የምትሰራው ሥራ አለ። ለሮቦቷ ሬዲዮ ማቋረጫ የ‹‹ሬዲዩ ጃመር›› ስርዓትም ተገጥሞላታል። ስለሆነም ሬዲዮ ማቋረጫ ሲስተም አገልግሎቱ የተወሰኑ ሬዲዮ ጣቢያዎች ያለፍቃድ እንዲቋረጥ ቢደረጉ፣ ሲስተማቸው ቢበላሽና በሌሎች ቁጥጥር ሥራ ቢገቡ የሬዲዮ ጣቢያዎቹ ትክክለኛ ያልሆነ ነገር እያስተላለፉ ከሆነ ሮቦቷ ወዲያወኑ በፍጥነት ሬዲዮ ጣቢያዎችን ከአየር



ተማሪ በንያስ ወንደወሰን

**ሮቦቷ አይኗ አካባቢ የፊት ገጽን ፎቶ የሚያነሳ ቁስ ተገጥሞላታል፤ በዚህም እንደ ፈለገች እየተሽከረከረች የአካባቢውን ፎቶ በማንሳት ደህንነት የመጠበቅ ስራዋን ትሰራለች**

ላይ በማውረድ እንዳይሰሩ ታደርጋለች።

ሮቦቷ ትክክለኛ ያልሆነውን የሬዲዮ ሞገድ እንዲቋረጥ በማድረግ በምትኩ ራሷ የምትፈልገውን መረጃ ታስተላልፋለች። በዚያ ወቅት በአካባቢው ላይ ያለ ማንኛውም ያንን ሬዲዮ የሚያዳምጥ ሰው የሚሰማው ድምጽ ሮቦቷ የምታስተላልፈውን መረጃ ብቻ ይሆናል። ተማሪ በንያስ እንደሚለው፣ ሮቦቷ በሬዲዮ ጣቢያዎች ላይ የነጣጠረ ጥቃት ሲፈጸም በፍጥነት ምላሽ በመስጠት ጣቢያው ያልሆነ ነገር ከማስተላለፍ እንዲቆጠብ ታደርጋለች። አድማጩም በተሳሳተ መረጃ ውዝግብ ውስጥ እንዳይገባ በማድረግ የምትጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው።

በተጨማሪም የድምፅ መረጃችን ለመሰብሰብ የሚያስችለው ‹ቮይስ እስፖ› ተገጥሟላታል። ሰዎች በአዳራሽ ተሰብሰበው በሚያወሩበት ጊዜ ሮቦቷ እዚያ አካባቢ ላይ እየተዘዋወረች ያሉትን ሰዎች የሚነጋገሩትን በመሰማት ድምጻቸውን በመቅረጽ (ሪከርድ) ለሚቆጣጠራት አካል ታስተላልፋለች። ይህም በ‹ቮይስ እስፖ› አማካኝነት ለመስማት የሚፈለግ መረጃ ካለ የትም ቦታ ላይ ሮቦቷን በማስቀመጥ የሚፈለገውን መረጃ በመሰብሰብ ለመቆጣጠር የሚያስችል ነው።

ሮቦቷ ያለማንም አጋዥ በራሷ ወዲያውኑ መሄድ እንድትችል ተደርጋ መስራቷን የሚገልጸው ተማሪ በንያስ፣ ሮቦቷ ራሷን ችላ በምትሄድበት ጊዜ አንዳንድ ያልተፈቀዱ ቦታዎች እንዳትገባ ለማድረግም መቆጣጠሪያ ተገጥሞለታል። ለሮቦቷ የመቆጣጠሪያ ስርአትም ተገጥሞላታል፤ ሲስተሙ የሚያገለግለው ማንኛውም ሰው ሮቦቷን እንደፈለገ መቆጣጠር እንዳይችል ለማድረግ እንደሆነም ተማሪው ይገልጻል።

እንደእሱ ማብራሪያ፣ አንድ ሰው ሮቦቷን ለመቆጣጠር ሲፈልግ የግድ ፍቃድ ማግኘት አለበት። ፍቃዱን ለማግኘት ደግሞ ለሮቦቷ የተሰጠውን የተጠቃሚ ስምና የሚስጥር ቁጥር ማወቅን ይጠይቃል። ሮቦቷን ማንኛውም ሰው ፍቃድ አግኝቶ የተጠቃሚ ስም እና የሚስጥር ቁጥሩን እስካላወቀ ድረስ ሮቦቷን ሊያዛት እንደማይችል ነው ያመለከተው።

ሮቦቷ የተሰጣትን ትክክለኛ የተጠቃሚ ስም እና የሚስጥር ቁጥር ከገባለት ግን ሥራዋን ወዲያውኑ እንደምትጀምር የጠቆመው ተማሪ በንያስ፣ ‹‹ሥራ ስትጀምር ሥራ መጀመሯን ለማሳወቅ አይኖቿ አካባቢ ያሉትን አረንጓዴ መብራት ታበራለች›› ይላል። ይህንን የምታደርገውም ‘ንቁ ነኝ፤ ለማገለገል ዝግጁ ነኝ’ ለማለት መሆኑን ይገልጻል። ይህም የምትጠቀምበት መግለጫ ቋንቋዋ እንደሆነ ነው ተማሪ በንያስ የሚያስረዳው።

በአጠቃላይ ይቺ ሮቦቷ ሁሉን የሬዲዮ ጃመር አይነቶች፣ ቮይስ እስፖ እና የተለያዩ የደህንነት መጠበቂያ ስርአቶች ስለተገጠመላት ሰዎች እነዚህን ስርአቶች ለሌላ ሕገወጥ ተግባሮች እንዳይጠቀሙባቸው ለማድረግ ደህንነቷን ለመጠበቅ የሚያስችል ሶፍትዌር ተገጥሟላታል ሲልም ያብራራል።

በሃርድ ዌር በኩልም የበር ላይ ቁልፍ በማዘጋጀት በሩ በሚከፈትበት ሰዓት ለባለቤቱ የሚጠቁም አሠራር እንደተገጠመላት ጠቅሶ፤ በባለቤቱ ስልክ ላይ በቀጥታ የመጠቆሚያ ድምጽ ለማሰማት መደወል የምትችልበትና ማስታወሻ የምትልክበት ስርአት የተገጠመላት መሆኗንም ነው ተማሪ በንያስ ያብራራል።

እንደተማሪው ገለፃ፡ ሮቦት አብዛኛው ኅብረተሰቡ ተጠቅምባቸው አያፈልጉም ብሎ ከጣላቸው ቁሳቁስ የተሰራች ናት፤ እነዚህን ቁሳቁስ መልሶ መጠቀም እንዲቻል አድርጎ በመገጣጠም ለሮቦቷ መስሪያነት አውሏቸዋል። ለምሳሌ ፕሮግራምድ የሚደረጉ ቦርዶች አሉ። እነዚህን ቦርዶች መልሶ በማደስ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚቻሉትን ሁኔታ ፈጥሯል፤ መልሶ መጠቀም የማይቻሉትን ደግሞ ገዝቶ ተጠቅሟል። የተጣሉ ሆነው ምንም ጥገና ሳይደረግላቸው መልሶ አግልገሎት ሊውሉ የሚችሉትን የተጠቀመበት ሁኔታም አለ።

የተማሪ በንያስ የፈጠራ ሥራ የሆነችው ይቺ ሮቦት ከሌሎች በውጭ ኀገራት ከተሰሩ ሮቦቶች በብዙ መልኩ ልዩነት አሏት። ተማሪ በንያስ እንደሚለው፤ እስካሁን የተሰሩትና አገልግሎት ላይ የዋሉት ሮቦቶች የተሰሩት አንድ አይነት አገልግሎት እንዲሰጡ ታስቦ ነው፤ በመሆኑም አንድ አይነት አገልግሎት ብቻ የሚሰጡ ናቸው። ለምሳሌ ለቤት ውስጥ ደህንነት አገልግሎት እንዲሰጥ የተሰራ ሮቦት አገልግሎት የሚሰጠው ለቤት ውስጥ ደህንነት መጠበቅ ብቻ ነው። ሌላ ተጨማሪ ሥራዎችን ሊሰራ አይችልም። ይቺ ሮቦት ግን በአንድ ጊዜ ብዙ አገልግሎቶች መስጠት ትችላለች። ‹‹የፈለግነውን ትዕዛዝ በመስጠት እንድትሰራ የምንፈልገውን ሥራ ማሰራት እንችላለን ››ይላል።

ሮቦቷ ውጭ ሀገር ከሚመረቱት ሮቦቶች አንጻር ስትታይ በዋጋም በኩል ቢሆን በተመጣጣኝ ዋጋ የምትሰራ መሆኗን ጠቅሶ፣ በአብዛኛው ጥቅም ላይ ከዋሉ ቁሳቁስ መሰራቷም በተመጣጣኝ ዋጋ ለመሰራቷ እንዱ ምክንያት መሆኑን ይገልጻል። ይቺን ሮቦቷን ሰርቶ ለማጠናቀቅ እስከ 50ሺ ብር ወጪ እንደተደረገም ተማሪ በንያስ አስታውቋል።

ይህ ታዳጊ የፈጠራ ባለሙያ በሳይበር ታለንት ማዕከሉ ከገባ በኋላ የሰራትን ይህችን ሮቦት ሰርቶ እንደ ጨረሰ እዚያ ላሉት የማዕከሉ አካላት አሳይቷል፤ “ሮቦቷን ሰርቼ ስጨርስ በማዕከሉ ላሉት አካላት ሳሳያቸው፤ በአድናቆት ተመልክተዋታል›› ሲልም ይገልጻል። ከዚያም ለሮቦቷ አስፈላጊ የሆኑ ፍተሻዎችና ሙከራዎች ተደርገው ጥቅም ላይ መዋል እንደምትችል ተረጋግጧል›› ይላል። ሮቦቷ የፍተሻ ሥራዋን እንደጨረሰች አገልግሎት ላይ መዋል እንደምትችል ታሞኖበት ለእይታ እንድትበቃ መደረጉንም ነው ያመለከተው።

በቀጣይ ሮቦቷን በማምረት ጥቅም ላይ የማዋል ሥራ እንደሚሰራ የተናገረው ተማሪ በንያስ፤ “ሮቦቶቹ ተምረተው በእያንዳንዱ ሰው ቤት በቤት ውስጥ ረዳትነት አለያም በተለያዩ የደህንነት ጥበቃ ሥራ ላይ አገልግሎት ሊሰጡ ይቻላሉ ብሎ አምናለሁ” ይላል።

አሁን የሰራት ሦስተኛዋ ሮቦት ቀደም ሲል በሙከራ ደረጃ ከሰራቸው ሁለት ሮቦቶች በብዙ መልኩ የተሻለ እውቀትና አቅም የታከለባት መሆኑን ይናገራል። ወደፊትም የተሻለ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የተሻለ ሥራ ለመስራት እቅድ እንዳለው ጠቅሶ፤ ልክ እንደሰው ልጅ ስሜትን የሚጋሩ እንደነሶፊያ ያሉ ሮቦቶችን የመስራት ፍላጎት እንዳለው ተናግሯል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

## በውስን ወቅቶች ተገድቦ የሚገኘውን የቱሪስቶች ፍሰት ስመለወጥ ምን ይደረግ?

**ስምስም መንግሥቱ**






የገና በዓልን በላልይበላ፣የጥምቀት በዓልን ደግሞ በጎንደር፣ በዓላቱና አካባቢዎቹ ተነጣጥለው የማይታዩ ናቸው። በእነዚህ የበዓላት ወቅት አስጎብኝ ድርጅቶች፣ሆቴልቤቶች፣መዝናኛዎች፣ ባህላዊ አልበሳትና ጌጣጌጥ መሸጫዎች፣ ሌሎችም ተያያዥ ሥራዎችን የሚሰሩ ሁሉ በዚህ ወቅት በስፋት ስለሚንቀሳቀሱ ቱሪዝሙ ይነቃቃል።

እንደ ሀገር በምጣኔ ሀብት እድገት ላይ ከፍ ያለ ሚና ይኖራቸዋል ተብለው ከተመረጡ አምስት የእድገት ምንጮች አንዱ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ነው። ቀደም ብለው የወጡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከዘርፉ በኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለመሆን፤እንደሀገር ሰባት ነጥብ አራት ሚሊዮን ቱሪስቶችን ለመሳብ ታቅዶ ሲሰራ ቆይቷል። የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ሰላምና መረጋጋትን ይፈልጋል።

ኢትዮጵያ ከዘርፉ የበለጠ ተጠቃሚ ለመሆን እየተንቀሳቀሰች ባለችበት ወቅት በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ተካሂዶ በነበረው ጦርነት፣ በሌሎችም አካባቢዎች ሰላምና መረጋጋት ባለመኖሩ ይህን ተከትሎም የተለያዩ ድጋፎች እንዳታገኝ በውጭ በተፈጠረባት ተጽእኖ፣ በዓለም ተከስቶ በነበረው ኮቪድ 19 ቫይረስ ወረርሽኝ ምክንያቶች እና ይህንኑ ተከትሎ የዓለም ሀገራት ለዜጎቻቸው የጉዞ ክልከላ ማድረጋቸው የቱሪስት ፍሰቱን በእጅጉ ቀንሶታል።

ኢትዮጵያ በዚህ ተግዳሮት ውስጥ ሆና ዘርፉን ለማንቀሳቀስ ጥረቶች ስታደርግ የቆየች ቢሆንም አሁንም ብዙ ሥራ ይጠበቃል። በተለይም ሰላም ማስፋትና ለቱሪዝሙ አቅም የሚሆኑ የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን እና መስህቦችን ማስተዋወቅ ይገባል።

ገናና የጥምቀት በዓላት ለዘርፉ መነቃቃት መልካም አጋጣሚዎች ናቸው። በዚህ ጊዜ በሀገር ውስጥም በውጭም ቱሪስቶችን በመሳብ ተጠቃሚ ለመሆን የተከናወኑ ስላሉ ተግባራት እንዲሁም ኢንዱስትሪው ከወቅታዊ እንቅስቃሴ ወጥቶ ዘላቂ እንዲሆን ምን መደረግ አለበት? ስንል የዘርፉን ባለሙያዎች አነጋግረናል።

የኢትዮጵያ ቱር ኦፐሬተርስ አሶሴሽን ፕሬዚዳንት አቶ ፍጹም ገዛኸኝ እንደገለጹት፤ኢትዮጵያ በውስጥ የገጠማትን የሰላም እጦት ተከትሎ ኤምባሲዎች የሚያሰራጯቸው እንዲሁም ሀገራት ለዜጎቻቸው የሚያስተላልፉት ማስጠንቀቂያዎችና የጉዞ ክልከላዎች የቱሪስቱን ከቦታ ቦታ የመዘዋወር ሁኔታ ገድቦታል። በዚህ ምክንያት የጉዞ ጥቅሎችን ለጎብኚዎች ለማቅረብ እና ቱሪስቶችን ለመሳብ ፈተና ሆኗል።

በየዓመቱ በገና እና የጥምቀት በዓላት ላይ ለመታደም አስቀድመው ምዝገባ ያካሄዱ ቱሪስቶች ጉዞአቸውን በመሰረዝ ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣው የቱሪስት ቁጥር እየቀነሰ ነው። ጥቂቶቹም ቢሆኑ የሚመጡት ቱር ኦፕሬተሮች ኃላፊነት እንደሚወስዱ በሚሰሩት ከፍተኛ የማሳመን ሥራ ነው። እየተደረጉ ያሉት ዝግጅቶችም ይመጣሉ ተብሎ በሚጠበቁ የእንግዶች ልክ ነው።

እንደ አቶ ፍጹም ገለጻ፤ ቱሪስቶችን ከተለያዩ ዓለማት ለመሳብ የአስጎብኝ ድርጅቶች(ቱር ኦፕሬተሮች) ድርሻ ከፍተኛ ነው። ቱሪስቱ በሚመቸው ጊዜ እንዲመጣ፣በመጓጓዣ፣በሆቴል፣በመዝናኛ አገልግሎቶች፣ ለሚያገኘው አገልግሎት ስለሚከፍለው ዋጋ፣ የሚጎበኛቸውን አካባቢዎች ጨምሮ የጉዞ ጥቅሎችን በማዘጋጀት አስቀድሞ በማሳወቅ ቱሪስቱን ለመሳብ ጥረት ያደርጋሉ።

ባለው ተሞክሮ ቱሪስቶች ለመጎብኘት የሚዘጋጁት ከሁለትና ከሶስት ዓመት በፊት ነው። ከያዙት ፕሮግራም ውጪ የሚንቀሳቀሱ ባለመሆናቸው ዛሬ ነገሮች ቢስተካከሉ በአንድ ጊዜ ተነስተው የሚመጡ አይደሉም። አሁን ባለው ሁኔታም ጉዞ የሚሰርዙ እንጂ ለመምጣት የሚዘጋጁ አይደሉም።

ጎብኚዎች ያለኢንሹራንስ ስለማይንቀሳቀሱ ከሀገራቸው ከመነሳታቸው በፊት የጉዞ ኢንሹራንስ ይገዛሉ። በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ከሀገራቸው ኢንሹራንስ ማግኘት ስለማይችሉም ጭምር ነው የማይመጡት። ኢንሹራንሳቸው ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሸፈንላቸው ለማድረግ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች የጉዞ ኢንሹራንስ እንዲሸጡ የሚያስችል ህግ የለም። ይህ ሁሉ ነው ለዘርፉ ተግዳሮት የሆነው።

አቶ ፍጹም እንደሚሉት አሁን አማራጩ ክፍተቱን ለመሙላት የሀገር ውስጥ ጎብኚዎችን በማበረታታት መጠቀም ነው። አንዳንድ አስጎብኚ ድርጅቶች ከተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ጎብኚዎችን በማነቃቃት ወደ ላልይበላ፣ጎንደርና ወደ ሌሎችም የቱሪዝም መዳረሻዎች በመውሰድ እና በመንቀሳቀስ ሁኔታዎችን ለመቀየር ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ።

የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ፤ ኮቪድ 19 ቫይረስ ወረርሽኝን ለመከላከል ክትባትን ጨምሮ የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በመሥራት ሁኔታዎች ከተስተካከሉና የፀጥታውም ሥጋት መጠነኛ ለውጦችን ካሳየ ወዲህ እንደሀገር የቱሪዝም እንቅስቃሴው መሻሻል እያሳየ መሆኑን ገልጸዋል።

በጦርነቱ የቱሪዝም ኢንዱስትሪው ተጎድቶ የነበረው በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል መሆኑንና ሰላም ባለባቸው የሀገሪቱ ክፍሎች በደቡብ ኢትዮጵያ፣በአዲስ አበባ ከተማም የኮንፈረንስ ቱሪዝም ጋር በተያያዘ በርካታ እንቅስቃሴዎች መደረጋቸውን አስረድተዋል። በሀገር ውስጥ ምቹ ሁኔታን መፍጠር ብቻ ሳይሆን፤ ተጽእኖ ፈጣሪ የሆኑ በውጭ ከሚገኙ አስጎብኚ ድርጅቶች ጋር በመሥራት ቱሪስቶችን እንዲልኩ ጥረት መደረጉን አቶ ስለሺ ጠቁመዋል።

በህዳር ወር በእንግሊዝ ሀገር በተካሄደው ዓለም አቀፍ የቱሪዝም የጉዞና የንግድ ጉባኤ ላይ ሚኒስቴሩ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር መሳተፉንና በዚህም ኢትዮጵያን በማስተዋወቅ፣የገበያ ዕድል በመፍጠር፣በዓለም መገናኛ ብዙኃንም መረጃዎችን በማድረስ ቱሪስቶችን ለመሳብ አጋጣሚውን መጠቀም መቻሉን አስረድተዋል።

በሀገር ውስጥም ቱሪስቶችን ተቀብለው የሚያስተናግዱ የተለያዩ አገልግሎት ሰጪዎች እንዲነቃቁ ስልጠና መሰጠቱን፣ ቱሪስቶች ከመጡ በኋላ የመረጃ መዛባት እንዳይፈጠር በኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ የቱሪስት መረጃ ማዕከል መቋቋሙን ገልጸዋል።

አቶ ስለሺ እንዳሉት፤ በዚህ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ ቱሪስቶች ገናን በላልይበላ፣ጥምቀትን ደግሞ በጎንደር ለማክበር ስለሚመጡ የአየር መጓጓዣ ችግር እንዳይገጥማቸው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር ቀድሞ በጋራ ምክክር አድርጓል። አየር መንገዱ አውሮፕላኖችን መድቦ 24 ሰአት ለመሥራት ዝግጁ መሆኑንም አረጋግጧል።

ከመስከረም እስከ ጥር ባሉት ወቅቶች ከፍተኛ ቁጥር ያለው ቱሪስት ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣበት ወቅት መሆኑንና በተለይም ገና እና ጥምቀት በዓላት በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ቱሪስቶች የሚታደሙበት፣ የቱሪዝም ኢንዱስትሪውም ከመቼውም ጊዜ በላይ የሚነቃቃበትና ዘርፉ ለኢኮኖሚው የሚያበረክተው ድርሻም ከፍ የሚልበት እንደሆነ ያለፉ ጥናቶችና መረጃዎች ዋቢ አድርገው ገልጸዋል። ከአውሮጳ፣ከአሜሪካን እና ከሌሎችም አካባቢዎች ትውልደ ኢትዮጵያውያንና ኢትጵያውያን ከፍተኛ ቁጥር ያለው ቱሪስት ይጠበቃል ብለዋል።

እንደ አቶ ስለሺ ማብራሪያ ቱሪስቶች በነዚህ ወቅት የሚሳቡት፤ በሌሎች የዓለም ክፍሎች የማያገኙት በዓል መሆኑ አንዱ ሲሆን ሌላው ገፊ ምክንያት የውጪዎቹ የራሳቸውን የገና በዓል እና አዲስ ዓመት ካከበሩ በኋላ የእረፍት ጊዜ ስለሚኖራቸው ለጉብኝትና ለመዝናናት ያውሉታል። ኢትዮጵያ ሳቢ የሆነ የቱሪስት መዳረሻ ስላላትም ቀዳሚ ምርጫቸው አድርገው ይመጣሉ። በገናና በጥምቀት በዓላትም በብዙ ሺ የሚቆጠር ቱሪስት እንደሚመጣ ተስፋ ተደርጓል።

በዘላቂነት ግን ሥራዎችን መሥራት እንደሚያስፈልግ የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ። በዚህ በላይ አቶ ፍጹም እንዳስረዱት፤ቱሪስቶች በተደጋጋሚ ጉዞ ሲሰርዙ ኢትዮጵያ የቱሪዝም መዳረሻ መሆኗን ከሚያመልከት ማፕ ላይ የምትሰረዝበት አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል። ይሄ ሁኔታ ከተፈጠረ ዘርፉን ወደነበረበት ለመመለስ ወይንም ቱሪስት ለመሳብ ረጅም ጊዜ ሊወስድና ዋጋ ሊያስከፍል ይችላል።

አሁን ላይ ቱሪስት ባይመጣ፤ለሚቀጥለው ይመጣል ብሎ ቀለል አድርጎ መውሰድ አይገባም። አስጎብኚ ድርጅቶች ላይም ሆነ በሀገር ደረጃ ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ በማሳጣት ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል ብለዋል።

ወቅትን ተከትሎ ቱሪስትን ለመሳብ ከሚደረግ እንቅስቃሴ ለመውጣት ሀገራዊ የንቅናቄ ሥራ ይጠይቃል። በዚህ ረገድም የኢትዮጵያ አየር መንገድን ጨምሮ በአየርና በየብስ የትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት ላይ የተሰማሩ፣ አስጎብኚ ድርጅቶች፣ሆቴልና መዝናኛዎች መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በአጠቃላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚሰሩ ባለድርሻ አካላት በአንድነት መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው እንደሚሉት፤ በቱሪዝም ኢንዱስትሪው ላይ የሚሰሩ ሌሎችም ሀገሮች ወቅታዊነትን ቀይረው ያልተቋረጠ የቱሪስት ፍሰት እንዲኖራቸው ማድረግ የቻሉት የዘርፉ ባለድርሻ አካላት በጋራ ንቅናቄ በመፍጠር ነው።

‹‹እንደ አንድ አስጎብኚ ድርጅት ወቅትን የተከተለ ሳይሆን ዓመቱን ሙሉ ቱሪስቶች ወደ ሀገራችን እንዲመጡ ነው የምንፈልገው። ዘርፉን ወቅታዊ ያደረገው አንዱና የመጀመሪያው የአየር ንብረት ሁኔታ ነው። የክረምት ወቅት ቱሪስት ለመሳብ ምቹ አይደለም። ቀድሞም ቢሆን የነበረው የመሠረተ ልማት አለመሟላት በክረምት ወቅት ለጉዞ የበለጠ አስቸጋሪ ነው። ስለዚህም ከመስከረም እስከ ጥር ያለው ወር ለቱሪስቶች ተመራጭ ነው።

ሌላው ዘርፉ ወቅታዊ እንዲሆን ያደረገው የገበያ ሁኔታ ነው። ገበያው ትኩረት ያደረገው በምዕራብ አውሮፓና ሰሜን አሜሪካን ባሉ ሀገሮች ላይ ስለነበር ነው። ከእነዚህ ሀገራት የሚመጡ ቱሪስቶችን መሳብ የሚቻለው ከመስከረም እስከ መጋቢት ባሉት ጊዜያቶች ነው። ከዚህ ውጪ ከነዚህ ሀገራት ገበያ ማግኘት አይቻልም። ›› ብለዋል።

አቶ ስለሺ እንደሚሉት በውስን ወቅቶች ተገድቦ የሚገኘውን የቱሪስቶች ፍሰት ለመለወጥ እና የገበያ እድል ለማስፋት በቱር ኦፕሬተሮች በኩል ከቱሪዝም ሚኒስቴር እና ኬሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የበኩላቸውን ሚና ሲወጡ ቆይተዋል።

በኢትዮጵያ የቱሪስት መሳቢያ ወቅቶች አይደሉም በሚባሉ ጊዜያቶች ቱሪስቶችን ሊያመነጩ ይችላሉ ተብለው በሚታሰቡ ደቡባዊ አውሮፓ ሀገሮች ጭምር በመሄድ እንዲሁም ክረምቱ ጠንካራ ባልሆነባቸውና የቱሪዝም መዳረሻ በሆኑ የኢትዮጵያ ክፍሎችን በመለየት፣ የቱሪስቱን አቅም ያገናዘበ የጉዞ ጥቅሎችን በማዘጋጀት ጭምር ቱሪስቱን ሊስቡ የሚችሉ የተለያዩ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ቱሪስቶችን ለመሳብ የተደረጉ ጥረቶች ይጠቀሳሉ።

በዚሁ ጉዳይ ላይ የኢትዮጵያ ቱር ኦፕሬተርስ አሶሴሽን ፕሬዚዳንት አቶ ፍጹም ገዛኸኝ እንደገለጹት፤ ዓመቱን ሙሉ የቱሪስት ፍሰት እንዲኖርና የቱሪዝም ኢንዱስትሪውን ዘላቂነት ለማረጋገጥ የተጀመሩት ሥራዎች ተጠናክረው እንዳይቀጥሉ ሀገሪቱን የገጠማት የውስጥ አለመረጋጋትና ከዚሁ ጋር ተያይዞም የተፈጠረው ጫና እና ተያያዥ ጉዳዮች ተጽእኖ አሳድረዋል።

ችግሮች ቢኖሩም ጥረቶች መቀጠል እንዳለባቸው የሚገልጹት አቶ ፍጹም፤ ‹‹ኢትዮጵያ እምቅ የቱሪዝም ሀብት ባለቤት ናት ማለት ብቻውን በቂ አይደለም ወደ ገንዘብ መለወጥ ያስፈልጋል። የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ሲኖራቸውና ማህበረሰቡም የጥቅሙ ተካፋይ ሲሆን ነው ትርፍ አግኝተንበታል ማለት የምንችለው ››ሲሉ አስረድተዋል።

እንደ አቶ ፍጹም ማብራሪያ፤ በዘርፉ ላይ የሚንቀሳቀሰው ሁሉ እያንዳንዱ ኃላፊነቱን ሲወጣና በቅንጅትም ሲንቀሳቀስ ነው ውጤት ማስመዝገብ የሚቻለው። አስጎብኚ ድርጅቶችም ያሉትን ቅርሶች በደንብ አውቀውና መዝግበው በዘርፉ ላይ በቂ እውቀት ኖሮአቸው የጉዞ ጥቅሎችን አዘጋጅተው ለገበያ ማቅረብ ሲችሉ ነው ቱሪስቶችን መሳብ የሚቻለው ብለዋል።

በዚሁ ጉዳይ ላይ ሚኒስትር ዴኤታው አቶ ስለሺ እንደሚያብራሩት ሰሜን አሜሪካና አውሮፓ ላይ ተንጠልጥሎ የቆየው ቱሪዝም ገበያ ወደ አፍሪካም ፊቱን እንዲያዞር የማድረግ ሥራ እየተሰራ ነው። አፍሪካ ውስጥ ትልቅ የቱሪዝም ገበያ እንዳለ ከኬንያ ተሞክሮ መውሰድ ይቻላል። ኬንያ ሁለት ሚሊዮን ቱሪስት ስትቀበል አንድ ሚሊዮን ቱሪስት የምትቀበለው ከአፍሪካ ሀገራት ነው። ኢትዮጵያ ግን እንዲህ ያለው ተሞክሮ አልነበራትም።

‹‹አፍሪካውያን የጋራ ታሪክ አለን፣ አፍሪካውያን አፍሪካውያንን ያፈቅራሉ የሚል እሳቤ ይዘን የአፍሪካ ገበያ ላይ እየሰራን ነው። በቅርቡ በሚካሄደው የአፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ ላይ የአፍሪካ መሪዎች ሲመጡ በጥሩ መስተንግዶ ለመቀበል ለአፍሪካ መሪዎች የሚሆኑ የተለያዩ የቱሪዝም ፓኬጆች ቀርጸናል። በአዲስ አበባና በዙሪያው እንዲጎበኙ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በቅርበት እንሰራለን››ሲሉ አስረድተዋል።

የአፍሪካ ኅብረት ስብሰባም ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው ትልቅ እድል ይፈጥራል ያሉት አቶ ስለሺ፤ ኢትዮጵያ የጥቁር ህዝቦችን ነፃነት ከማረጋገጥ፣የአፍሪካ ኅብረትም እንዲመሰረት አስተዋጽኦ ከማበርከት አንጻር ትልቅ ታሪክ እንዳላት ገልጸዋል።

በተለያየ ምክንያቶች የተጎዳውን የቱሪዘም ኢንዱስትሪ ለማነቃቃት ሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲረባረቡ የዘርፉ ባለሙያዎች ጥሪ አቅርበዋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# « የሚያነብ ትውልድ ሀገር ማጎልበት ላይ የዝሆንን ድርሻ ይወስዳል »

**ሰሚራ በርሀ**

ሀላባ ካፈራቻቸው ውድ ልጆቿ መካከል አንዷ ናት። ሀላባ ውስጥ በምትገኝ አቦምሳ በምትባል ትንሽዬ ከተማ ውስጥ ነበር የተወለደችው። መምህራን ከሆኑ ወላጆች የተወለደችው የዛሬ እንግዳችን በልጅነቷ የአስተማሪ ልጅ አርአያ መሆን አለበት በሚል መርህ ጎበዝ በመሆን ከፊት መስመር ተሰላፊ ነበረች።

ማክዳ ሁሴን አርሺ ትባላለች። በሙያዋ ነርስ ናት። ባለትዳርና የሶስት ሴት ልጆች እናት ስትሆን የልጆች መጽሀፍ ትጽፋለች። ኑሮዋን ያደረገችው በአሜሪካ የቨርጂኒያ ግዛት ነው። ሀገር ወዳድ የሆኑ እና ብቁ ዜጎችን ማፍራት የሚቻለው ልጆች ላይ በመስራት ነው የሚል ሀሳብ አላት። በንባብ የዳበረ አዕምሮ ትልቅ ዋጋ አለው የሚለው ሀሳብም በእጅጉ አትኩሮት የምትሰጠው ጉዳይ ነው። በቅርቡም «the world needs a uniquely happy you » መጽሀፍ የጻፈች ሲሆን ይህ መጽሀፍ ወደ አማርኛ « የዓለም መብራቶች » በሚል ተተርጉሟል ። በዛሬው የሴቶች ገጻችን ስለጻፈችው የልጆች መጽሀፍ ፣ ስለልጆች አስተዳደግ እና የህይወት ልምዷን እንድታጋራን እንግዳችን አድርገናታል ።


አባቷ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ፤ እናቷ ደግሞ የሒሳብ መምህር ናቸው። የማክዳ ወላጆች መምህራን በመሆናቸው በተለያዩ ቦታዎች ተዘዋውረው ስራቸውን ሲያከናውኑ ማክዳም ከእህትና ወንድሞቿ ጋር አብራ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ተዘዋውራ ኖራለች። በአርሲ ክፍለ ሀገር ሳጉሬ የምትባል ከተማ ፣ በናዝሬት ከተማ ኑሯቸውን አድረገዋል። ማክዳም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በሀላባ ከጨረሰች በኋላም ወደ አዲስ አበባ መጡ። ማክዳ የጽሁፍ ዝንባሌዋ ከልጅነቷ ጀምሮ የነበረ ነው። በትምህርት ቤት ውስጥ በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተለያዩ ጽሁፎችን ትጽፋለች። ይህን የመጻፍ ዝንባሌዋን የተመለከቱት አባቷም ወደፊት የስነ-ጽሁፍ ሰው ልትሆን እንደምትችል ይነግሯት ነበር። የመጻፍ ክህሎቷም ጥሩ በመሆኑ በትምህርት ቤት ውስጥ ካሉ የቋንቋ መምህራኖቿ ጋር ጥሩ ግንኙነት ነበራት ።

ማክዳ ወንድምና እህቶች የወላጆቻቸውን ፈለግ በመከተል ወደ መምህርነት ሙያ ሲያቀኑ ማክዳ ወደ ጤናው ዘርፍ የገባቸው ከሌላ አንድ እህቷ ጋር ነበር ። የነርሲንግ ትምህርት (አዋላጅ ነርስ )ለመማር ምክንያት የሆናት አጋጣሚ በልጅነቷ የምታስታውሰው ነበር ። በአሰላ ከተማ ውስጥ የሷ መኖሪያ እና የአሰላ ሆስፒታል ቅርብ ለቅርብ ናቸው። እናም በአሰላ ሆስፒታል ውስጥ የሚገኙ የጤና ባለሙያዎች ነጭ ጋወናቸውና የልብሳቸው ጸዓዳነት ነርስ መሆንን እንድትመኝ አደረጋት። ማክዳም የምትፈልገውን ነገር አገኘች። የመሰናዶ ትምህርቷን ስትጨርስ በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የህክምና ሳይንስ ኮሌጅ የነርሲንግ ትምህርት ክፍልን ተቀላቀለች። « አባቴ እንደሚለው በጊዜው ወደ ቋንቋ እና ወደ ስነ-ጽሁፍ ባደላም። ነገር ግን ይበልጥ መማር የምፈልገው ነርሲንግ ነበር » የምተለው ማክዳ ዩኒቨርሲቲ በነበረችበት ወቅትም የጽሁፍ ዝንባሌዋን አልተወችውም ።

ትምህርቷን ስትጨርስ በዚያው በጎንደር ከተማና ፣ ባደገችበት የሳጉሬ ጤና ጣቢያ ሰርታለች ። ከዛ በመቀጠል በመካከለኛው ምስራቅ ዱባይ የሰራች ሲሆን አሁን ወደ አሜሪካን ሀገር ተጉዛ ኑሮዋን በቨርጂኒያ በማድረግ በነርሲንግ ሙያ እያገለገለች ትገኛለች ። የነርሲንግ ሙያ ለማክዳ ከእናትነት ቀጥሎ ልገልጸው ቃላት ያጣሁለት ሙያ ነው ትላለች። « የነርሲንግ ሙያ ማለት ሰው አንቺ ጋር የሚመጣው በደከመበት ባቃተው ሰዓት ነው ። ያ ደግሞ ትልቅ ኃላፊነት ነው። »

ማክዳና ቤተሰቦቿ በተለያዩ ቦታ ተዘዋውረው ይኑሩ እንጂ የማክዳ እናት ግን ከሀገር ወጥቶ መኖርን የምትደግፍ አልነበረችም። ሁሉም ሰው በሀገሩ ሰርቶ መለወጥና ማደግ ይችላል የሚል አቋም ነበራት። ነገር ግን ማክዳ በስራ እና በትዳር ህይወቷ አጋጣሚ ከሀገር ወጥታ ስትኖር ከ13 አመት በላይ ሆኗታል። ማክዳ በስራዋ ነርስ ስትሆን የምትኖርበት ሀገር የስራ ባህል እና የኑሮ ሁኔታ ከልጆች ጋር በቂ ጊዜ ለማሳለፍ ምቹ አለመሆኑን ታነሳለች ። በመሆኑም ከቤታቸው ውጪ በስራ አለም የተሰማሩ ሴቶች ልጆቻቸውን ለማሳደግ ቤት መሆን ፣ አልያም ደግሞ ልጆቻቸውን ቤት ትተው ስራ ለመስራት የቱን መምረጥ እንዳለባቸው ሲወዛገቡ አስተውላለች። አንድ በስራ አለም ላይ ያለች ሴት የልጆች እናት ስትሆን የሚደርስባትን ውጥረትም በራሷ እንደተመለከተችው ትናገራለች ።

ማክዳ (The world needs a uniquely happy you



ማክዳ ሁሴን አርሺ

) የአማርኛ ትርጉሙ « የዓለም መብራቶች » በሚል በቅርቡ ለንባብ ያበቃችውን የልጆች መጽሀፍ ለማዘጋጀት ምክንያት የሆናት አጋጣሚ ሶስተኛ ልጇን ወልዳ በቤት ውስጥ አራስ በነበረች ጊዜ ከወሊድ በኋላ ያለው ድካም ልጅን መንከባከብ ይህ ሁሉ ተጨምሮ ደግሞ በወሊድ እረፍት ምክንያት ትታ የመጣችውን ስራ እንኳን በአራስ ቤት ውስጥ ሆና ለመስራት የተገደደችበት ወቅት ነበር። ታዲያ ይህን መጽሀፍ ስትጽፍ ልጇን ለማጥባት በምትነሳበት ወቅት ልጇ ተኝታ ከዚያም ድጋሚ ከእንቅልፏ እስከምትነሳ ድረስ መጽሀፏን መጻፍ ጀመረች ።

ማንኛዋም ሴት ኑሮዋና ፍላጎቷን ባማከለ መልኩ የምትፈልገውን ነገር ደስ እያላት ልታደርገው ይገባል። አንዷት ሴት በአሁን ሰዓት ስራም ሰርታ ገንዘብ ለማምጣት ቤት ውስጥ እናት ለመሆን ፣ ሚስት ለመሆን እነዚህ ሁሉ ሀላፊነቶች አሉባት ። የምትለው ማክዳ ይህን ሁሉ ለማድረግ በነበራት ውጥረት ውስጥ ያስተዋለችውን ነገር ጤናማ እናት ሆና ለመኖር እና ጥሩ ዜጋ ለማፍራት ማድረግ የምችለውን መገደብ ያስፈልጋል ። « ልጆቿን ቤት ውስጥ ቁጭ ብላ ማሳደግ የምትፈልግ እናት ብትኖር ደስ እያላት እንድታደርገው ፣ ልጆችም ወልዳ ስራ መስራት ግድ የሚላት የህይወት መስመር ላይ የምትገኝ እናትም ደስ እያላት እንድትሰራው ትመክራለች።

መጽሀፉ ልጆችን በምን መልኩ ማሳደግ እንደሚገባ ፍላጎታቸውን እና ዝንባሌያቸውን እያየን በሚፈልጉት መልኩ ራሳቸውን እንዲያሳድጉ እንዴት መንገድ መምራት ይገባል የሚለውን ያካትታል ። ብዙውን ጊዜ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ልጆች ትምህርት ተምረው እኛ በምንፈልገው መስክ ብቻ እንዲያድጉ ነው የምናደርጋቸው። ነገር ግን ልጆች ስሌላው የህይወት ክፍል ሳያውቁ ያድጋሉ ያ ደግሞ ልጆች አድገው ከህይወት ጋር በሚኖራቸው ግብግብ የስነልቦና ቀውስ ይፈጠርባቸዋል። ስለዚህም ትላለች ማክዳ ልጆቻችንን ስናሳድግ እንደየ እድሜያቸው የሚደርሱበትን ሀላፊነት ምንማለት እንደሆነ እንዴት እንደሚወጡት እየነገርናቸው ማሳደግ ይገባናል ትላለች። ልጆቻችን በሚሰማሩበት ቦታ ሁሉ እኩል አስተዋጽኦ እንዳላቸው መንገር ያስፈልጋል።

በመጽሀፉ ላይ ከሰባት የሚበልጡ የተለያየ ሙያላይ የተሰማሩ ገጸ-ባህሪያት ይገኛሉ ። ልጆች ያላቸውን ዝንባሌ ከልጅነታቸው ጀምሮ በማየት በልጅነታቸው ፈልገው የሚያደርጉትን ነገር በማጎልበት አድገውም በልጅነታቸው የሚፈልጉትን ነገር ሆነውት ማሳየት ነው ። ከዚያም እነዚህ ጓደኛማቾች አድገው በሙያቸው በማንነታቸው ሳናናቁ ተዋደውና ተከባብረው ዘልቋል ጓደኝነታቸው አንድነትን ለመሳየት በመጽሀፉ ላይ ተሞክሯል።

ከሀገር ከወጣች 13 ዓመት የሆናት ማክዳ በየእለት ተዕለት ኑሮዋ በአብዛኛው ማለት በሚቻል የምትጠቀመው እንግሊዘኛ ቋንቋን ነው። በመሆኑም መጽሀፏን በእንግሊዘኛ ቋንቋ እሷ ስትጽፈውና ስታዘጋጀው ወደ ሶስት ወር ገደማ የፈጀባት ሲሆን ዘጠኝ ወር ለሚሆን ጊዜ ደግሞ የአርትኦት ስራው ሲሰራ ቆይቶ ለንባብ ሊበቃ ችሏል። ለልጆች የሚያነቡት በመሆኑ በጥንቃቄ ዝግጅት ተደርጎበታል።

መጽሀፉ ልጆችን በምን መልኩ ማሳደግ እንደሚገባ ፍላጎታቸውን እና ዝንባሌያቸውን እያየን በሚፈልጉት መልኩ ራሳቸውን እንዲያሳድጉ እንዴት መንገድ ማሳየት ይገባል የሚለውን ያካትታል። መጽሀፉ ለንባብ ከበቃ በኋላ ጥሩ ተቀባይነትንም አግኝቷል። « እኔ ነኝ እንዴ የጻፍኩት እስከምል ድረስ በጣም ጥሩ ተቀባይነትን አግኝቻለሁ። በተለይ ደግሞ በዚያ ሀገር የሚኖሩ እናቶች ወደውታል » ህብረተሰቡ ሴቶች ላይ ጫን ይላል የምትለው ማክዳ ሴቶች መሆን የሚፈልጉትን የሚያበረታታ ስለሆነ ራሳቸውን በገጸ-ባህሪያቱ ውስጥ እንዳገኙትም ነግረዋታል። በቤታቸው ፣ በቤተ-መጽሀፍቶች በትምህርትቤቶች ውስጥ እንዲሁ እንዲቀመጥ መርጠውታል ። ስትል ያለውን ተቀባይነት በደስታ ትገልጻለች ። ማክዳ በህይወቷ የሚገጥሟት ፈተናዎች ወይንም አሉታዊ ነገሮችን ማንሳት ባትፈልግም መጽሀፏን በምትጽፍበት ወቅት ግን ጊዜ ያጥራት እንደነበር ትናገራለች ።

መጽሀፉ በአንባቢያን ዘንድ ተቀባይነትን ከማግኘት ባሻገር ሶስት ሽልማቶችን እንዲሁ አሸንፏል። (the world needs a uniquely happy you ) የእንግሊዘኛ ርዕሱ ሲሆን « የዓለም መብራቶች » የአማርኛ ትርጉሙ ነው። ማክዳ « የተሸለምኳቸው ሽልማቶችም ይበልጥ እንድጽፍ ያበረታቱኛል » ትላለች ። ( mama`s choice award ) ( በእናቶች ምርጫ አዋርድ ) የመጀመሪያ ሽልማት ሲሆን በሴቶች የሚመራ ድርጅት ሆኖ ላለፉት ሀያ አመታት ለቤተሰብ የሚሆኑ ስነ-ጽሁፎችን እየመረጠ ሽልማት ይሰጣል። የማክዳ መጽሀፍም የጎልድ ሲል አዋርድ ለማሸነፍ ችላለች ። ሁለተኛው ሽልማት ደግሞ (royal dragon fly book award )ስቶሪ ሞንስተርስ በሚል ዘርፍ አሸንፋለች ። ሶስተኛው ሽልማት ደግሞ በምርጥ ተነባቢ መጽሀፍ ሽልማት ተበርክቶላታል።

መጽሀፏን ጽፋ ለንባብ እንዳበቃችም በእውቁ የአማዞን ገበያ ላይ ለሽያጭ መቅረብ ችሏል ። በአማዞን ላይ እጅግ በጣም የታዋቂ ሰዎች መጽሀፍት ይገኛሉ። ማክዳም መጽሀፋን እዚህ ላ ለማስቀመጥና በአለምቀፍ ደረጃ ያሉ ወላጆች ጋር እናቶ፡ች ጋር እንዲደርስ በማሰብ ለአማዞን ብቁ ነው ለመባል የሚያስችሉ መመዘኛዎችን ካለፈች በኋላ መጽሀፏን ለማስቀመጥ ችላለች።

በመጽሀፉ ላይ የተካተቱት ገጸ-ባህሪያት የተለያየ አለም ላይ ያሉ ባህሎችን የሚወክሉ በመሆናቸው በራሳችን ቋንቋ ልጆቻችን ስለሌላው ዓለም ታሪክና ባህል ፣ ቴክኖሎጂን እንዲያውቁ ማድረግ እንችላለን በማለት ወደ አማርኛ ቋንቋ ተተርጉሟል። ከዚህም ባሻገር በሀገራችን ያለው የልጆች መጽሀፍ በቁጥር አናሳ በመሆኑ ሌሎችን ከመውቀስ ይልቅ የመፍትሄ አካል መሆንን መርጣለች ። የልጆች መጽሀፍትን የሚጽፉ ደራሲያን መጽሀፎቻቸውን ልጆችን በሚጋብዝ መልኩ እንዲያዘጋጁት ስትልም ሀሳቧን ታካፍላለች ።

በእንግሊዘኛ ቋንቋ ተቀባይነትን ያገኘው መጽሀፍም « የዓለም መብራቶች » በሚል ወደ አማርኛ ተተርጎሟል። መጽሀፉን ጋዜጠኛ አንተነህ ከበደ የተረጎመው ሲሆን \ አርትኦት ስራውን ደግሞ ደራሲ ኃይለመለኮት መዋዕል ሰርተውታል። በምርቃት ስነ-ስርዓቱ ላይም አንድ ሜትር ከ30 ቁመት እና አንድ ሜትር ስፋት ያለውን አማርኛውንም እንግሊዘኛውንም መጽሀፍ በጋራ የያዘ ሲሆን ለልጆች በሚስብ መልኩ እንዲታያቸው ታስቦ የተዘጋጀ ነው። መጽሀፉ ልጆችን ታሳቢ አድርጎ የተዘጋጀ በመሆኑ ህጻናት ሊወዱት በሚችል መልኩ በቀለማት ያሸበረቀ ሆኖ የተዘጋጀ ነበር። ህጻናት የማንበብ ፍቅራቸው እንዲዳብር መጽኅፍን ደስባላቸው እና ደስተኛ በሆኑበት ጊዜ ብንሰጣቸው መጽሀፍን ደስ ከሚለው ስሜት ጋር ያያይዙታል በማለት ከመጽሀፍ ጋር ያላቸው ቁርኝት እንዲዳብርም ጭምር የታለመ ነበር ።

ማክዳ ለሚያነብ ሰው በሮች ሁሉ ክፍት ናቸው የሚል ሀሳብ አላት። በእስልምና እምነትም ቢሆን ነብዩ መሀመድ የተባሉት የመጀመሪያው ትእዛዝ አንብብ ነው ስትል ትገልጻለች « ማንበብ ሙሉ ሰው ያደርጋል ሲባል አባባል ብቻ አይደለም ሙሉ ሰው ስለሚያደርግ ነው። » ትላለች ማክዳ በምትኖርበት ሀገር እና ተወልዳ ባደገችባት ኢትዮጵያ ንባብን የተመለከተ ሰፊ ልዩነት ስለመኖሩ ታነሳለች። መጽሀፎች በተለያዩ ቦታዎች በቀላሉ ይገኛሉ። በኛ ሀገር ግን ማንበብ ወደ ጎን የተተወ ይመስላል ስትል የታዘበችውን ትገልጻለች። « ልጆች ማንበብን እንዲወዱ እና ባህላቸው እንዲያደርጉት ወላጆች አብረዋቸው ሊያነቡ ይገባል። ምክንያቱም ህጻናት የምንናገረውን ሳይሆን የምናደርገውን ነው የሚመለከቱት» ትላለለች። ልጆች የሚያድጉበት መንገድ እና ሳይንስ ከጊዜ ወደጊዜ እየተቀያየረ ነው የምትለው ማክዳ ልጆቿን ለማሳደግ የምትኖርበትን ሀገር የልጅ አስተዳደግ ባህል መማር ማወቅ እና ልጆቿን በዛ መንገድ ከራሷ አስተዳደግና ባህል ጋር አጣምራ ታሳድጋለች ። ባለንበት ዘመን የተለያዩ ባለሙያዎች ባጠኑት ጥናት ሰዎች ህጻናት በእናታቸው ማህጸን ሳሉ ከአባት ወር ጀምሮ ድምጽን ይሰማሉ የሚል ነው። ማክዳም ልጆቿ መጽሀፍ ማንበብን ለምዳቸው እንዲያደርጉ ከእርግዝና ጊዜዋ ጀምሮ ይህንን ታደርግ እንደነበር ታስታውሳለች።

በቅድሚያ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ተጽፎ መጽሀፍ ወደ አማርኛ የተተረጎመው የማክዳ መጽሀፍ በተለያዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ተተርጉሞ ለአንባቢያን ለማድረስ እየተሰራ ይገኛል። በትግርኛ እና በኦሮምኛ ቋንቋ የትርጉም ስራው ያለቀ ሲሆን በሶማልኛ ፣ በአፋርኛ እና ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎም ለሚፈልጉ ሰዎች ማክዳ ጥሪዋን ታቀርባለች ።

« ለመስራት የደከምኩባቸው በቃኝ ያልኩባቸው ጊዜያት ነበሩ ነገር ግን በስራዬ የሚያግዘኝ የትዳር አጋር ተሰጥቶኛል » የምትለው ማክዳ እናቶች የምናበረክተው ነገር ሁላችንም ጋር አለ « የውሀ ጠብታም ብትሆን ዛሬ ላይ የምናደርገው ነገር ነገ ለልጆቻችን ስለሚጠቅም ዝም አትበሉ የሚያነብ ትውልድ ሀገር ማጎልበት ላይ የዝሆንን ድርሻ ይወስዳል። » የምትለው ማክዳ ማንበብ በአዕምሮ እድገት ላይ በቤተሰብ ፍቅር ላይ ፣ በሀገር ሰላም መሆን ላይ ትልቅ ድርሻ አለው። ስትል ትገልጻለች ። ስለዚህም ልጆቻችን እንዲያነቡ በማድረግ ነገም እንዳንወቅሳቸው እኛም እንዳናለቅስ የሚያነብ ዜጋ እንድንፈጥር አብረን እንስራ የሚል መልእክቷን ታስተላልፋለች።

ማክዳ ከትዳር አጋሯ ዶክተር ኢስማኤል ኢድሪስ ዩሱፍ በትዳር 20 አመት ቆይተዋል። ሶስት ሴት ልጆችንም አፍርተዋል። በእነዚህ ጊዜያት ዘመም ስል ቀና እያደረገ በህይወቴ ትልቅ ድርሻ አለውና ክብር ይገባዋል ትላለች።

በሀገር ውስጥ የነበረውን የመጽሀፍ ምርቃት ያማረ እንዲሆን የተባበሯትን ፣ መጽሀፉን በጥንቃቄ በማተም ፓክ ፐርፌክት ፓኬጂንግ እና ፕሪንቲንግ እንዲሁ አመስግናለች።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

**መቼም በገና ጨዋታ አይቀጡም ጌታ ነውና ነገሩ ፤"ገና እንዴት አለፈ?" ይለናል የ1964ቱን የገና በዓል አከባበርን ስዛሬው አዲስ ዘመን ድሮ ሲተርክልን ፨ ፨ ፨ የበዓሉን ድምቀት ከነ ዶሮና ጠጁ ከትረካው ጋር በምናብ ትውስታ እያጣጣምን።**

**ከበዓሉ መንደር ወጣ ስንል ደግሞ በአዲስ አበባ የሚገኙት ቤቶች በሙሉ አንድ አይነት ቀለም እንዲቀቡ ትዕዛዝ ወጥቷል። ውሻ ሰውን ነከሰ ማለቱ ቀርቶ፤ ውሻውን ነክሶ የተከሰሰው ግለሰብ ለፍርድ ቀርቧል። ከዚህ ሳይ የጳውሎስ ኞኞን ደብዳቤ ጣል በማድረግ ሁሉም ከየፈርጁ ተሰናድተዋል።**

### ገና እንዴት አለፈ ?

ከእስክንድሪያ በመጣው ፍሬምናጦስ ምስክርነት ከ3ሺህ 133 ዓመተ ምሕረት ጀምሮ መከበር የጀመረውና በራሳችን አቆጣጠር ታኅሣሥ 29 የሚውለው በዓለ ልደት በቀደምም አንድ አክሎ አልፏል።

....

በነብይ ከጌታ ዘንድ "እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች። ስሙንም አማኑኤል ይሉታል" የተባለው ይፈፀም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኗል ከሚለው የቅዱስ መጽሐፍ አገላለጽ የምንረዳው ይህንኑ ነው። ታስቧል፤ ይታሰባል።

ይህንን ክንውን ዞሮ መመልከቱ ደግ ነበር። ሆኖም "ደም በፈሰሰበት ዓውደ ዓመት ከቤት አትውጡ" የሚለው የአያቴና የእናቴ ልማድ በድምጽ ብልጫ አሸነፈ። ያም ሆነ ይህ፣ ገና እንዴት አለፈ?

"በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ" የተባለለትን የድሮ ዘመን በትዝታነቱ ትተን ዛሬ ላይ እናተኩራለን። በዋዜማው የተለያዩ ትላልቅ ሆቴሎች፤ ሌሎችም እንዳቅማቸው ሙዚቃና ቡፌ ደግሰዋል። የዚያን ቀንም እንደወትሮው ብዙ ወጣቶች ድምፅ ማጉያ ጨብጠው ዕውቅ ድምፃውያንን ለመምሰል ሲውተረተሩ ተስተውሏል። ለየት ያለ ዝግጅት ካቀረቡት መሐል አንጋፋው ያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት አንዱ ነው። በዚያ የመገኘት ዕድሉ ገጥሞን ነበር። ከሁለት ሰዓት ያነሰ በፈጀው በዚሁ ድግስ ሶሎ ኮንሰርት፣ ያሬዳዊ ዝማሬ፣ የአማርኛ ግጥሞች፣ ባሕላዊ ሙዚቃ እና ፖፕ ሙዚቃዎች የቀረቡ ሲሆን፣ በተለይም የኅብረት ዝማሬዎች በአብዛኛው የልደትን በዓል የሚያመለክቱ፤ የበዓሉንም ትልቅነት የሚያበስሩ ነበሩ።

....

ይህንን በዚሁ አጠናቀን ስንወጣ በፆም የከረሙት የክርስትና እምነት ተከታዮች፤ በተለይም የኦርቶዶክስ አማኞች ሌሊቱን ሙሉ በየቤተክርስቲያኑ በምሥጋና ያነጉ ሲሆን፣ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘ ኢትዮጵያ ቡራኬ ሰጥተዋል።

....

በ24 ሰዓት አገልግሎቱ የታወቀውና በእንግሊዝ ግዙፍ የዜና ማሰራጫ የሆነው ቢ-ቢ-ሲ "ኢትዮጵያን በትኩረት" በሚል ርዕስ ስለ ገና በዓል ሰፋ ያለ ዝግጅቱን በማለዳ ሞገድ አስደምጧል።

የገናን በዓል ካጀቡት ሌሎች አስገራሚ ትዕይንቶች መሐል አንዱ የጋዝ ሰልፍ ነበር። ከአራት ኪሎ ቶታል እስከ ቱሪስት ሆቴል የነበረው ወረፋ በወቅቱ አጠያይቋል። ከየቤቱ ሰው የቀረ አይመስልም። ምኒልክ አደባባይ ሞቢል ደርሰን አቶ ደረጀ ዓለማየሁ እንዳጫወቱን ከሆነ የጋዝ እጥረት የለም። በእርግጥ አንዳንድ ቦታዎች ስላለቀና ዓመት በዓልም ስለሆነ ግፊያው አይሎ ሊሆን ይችላል። .

ሌላው ያነጋገረ ጉዳይ ደን ነው። በዚህ ዓመት ጥድ አልተረፈም። "አንድ ዛፍ ከመቁረጥህ በፊት ሁለት ችግኞችን ትከል" ያለው የአካባቢ ጥበቃ ድርጅት የመስቀል አደባባይን ንግድ አለማየቱም ደግ ነገር ነው። ለማንኛውም መምሰል አይከለከልም፤ ግን 4 በመቶ ቀርቶታል የተባለውን የሀገራችን የደን ይዞታ ወደ ነበረበት ከመመለስ ጨርሶ ማጥፋቱ ይቀላል ተባለ እንዴ?

መቼም በዓል ተተርኮ አያልቅም፤ ግን በዘንድሮው ገና የራሱ ዜማም በማትረፍ በይበልጥ ሳይደምቅ አልቀረም። በአምባሰል ሙዚቃና ቪዲዮ መደብር አሳታሚነት ገበያ ላይ የዋለው የመስፍን አበበ ካሴት እንዲህ ብሏል።

ብሩህ ሰማይ፤ ብሩህ ዕለት
መልካም በዓል፤ መልካም ልደት
ላከበረው የደስታ ቀን ይሁንለት

**(አዲስ ዘመን ጥር 1 ቀን 1987 ዓ.ም)**

### በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙት ቤቶች ተመሳሳይ ቀለም እንዲቀቡ ትእዛዝ ተሳለፈ

በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙት መኖሪያ ቤቶች፣ የንግድና የሌላም ዓይነት ተግባር ማከናወኛ መደብሮች ከዚህ ወር ጀምሮ ለአካባቢው የሚስማማ ቀለም እንዲቀቡ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ማሳሰቢያ ተሰጥቷቸዋል። ይህን ማሳሰቢያ የሰጡት ክቡር ሚኒስትር ኃይለ ጊዮርጊስ ወርቅነህ፣ የአዲስ አበባ ከንቲባ ናቸው።

......

የሚቀቡትም ቀለም አልባሌ ሳይሆን በየዓይነቱና በጥራቱ የተሻለ መሆን አለበት። የቀለሙንም ዓይነት በየክፍሉ የሚገኙ ማዘጋጃ ቤቶች ሊሰጡ ይችላሉ ሲል የማዘጋጃ ቤቱ የማስታወቂያና የሕዝብ ኅብረት ማስፋፊያ ክፍል በተለይ ለአዲስ ዘመን ገልጿል።

የአዲስ አበባ ከተማ በአየርና በከፍተኛ ሥፍራ ሆነው ሲያዩት አብዛኛውን ቤት ጣራው የቆሸሸ፤ ቀለሙ የዛገ ሆኖ ይታያል። ስለዚህ እንደ ባለቤቱ መራጭነት አረንጓዴ ወይም በቀይ ቡናማ ቀለም መቀባት አለበት የሚል ማሳሰቢያ ክቡር ከንቲባው መልዕክት ውስጥ ይገኛል። ያረጀውም ጣሪያ እንዲለወጥ የክፍሉ ባለሥልጣኖች በጥብቅ ታዝዘዋል።

**(አዲስ ዘመን መስከረም 7 ቀን 1964ዓ.ም)**

### ሰው ውሻ ነክሶ ተቀጣ

ኒውተን ዲስተር የሚባል አንድ የሚዙሪ ተወላጅ ሹሺ የሚባል የጎረቤቱን ሰዎች የውሻ ቡችላ ነክሶ ተከሶ በውሻዋ ላይ ስለፈጸመው የነከሣ ወንጀል 3 መቶ ብር ተቀጥቷል።

በንክሻ ወንጀል ክሱን የመሠረተችው ሉሉ የምትባለዋ የውሻዋ ባለቤት፤ ለፍርድ ቤቱ ስታስረዳ፤ ፎስተር ለብዙ ጊዜ ጨዋ ጎረቤታችን ነበር፤ ከውሻዋም ጋር ይዋደዳሉ። ከጊዜ በኋላ የመጣበት የውሻ መንከስ ጠባይ ለእኛም ስለሚተርፍ ሠፈሩን ለቅቆ ይውጣልኝ በማለት አመለከተች።

**(አዲስ ዘመን ጥር 5 ቀን 1964 ዓ.ም)**

### አንድ ጥያቄ አለኝ
### ይድረስ ለጳውሎስ ኞኞ

*ጅብ የሚጮኸው ወደ መሬት አጎንብሶ ነው፤ ቀና ብሎ የጮኸ እንደሆን ሰማዩ ይሰነጠቃል የሚሉት እውነት ነው?

ፍሥሐ ማን ዱባለ (ከካራቆሬ)

-ውሸት ነው። እንኳን ሰማይ ሊሰነጥቅ ግድግዳም አይበሳ።

ወይዘሪት ሰብለ ካሣ

-እምዩ ብዙ ሰው እንደ ድመት ጭራውን የሚቆላው የሚፈልጋት ጣፊያ እስኪጣልለት ድረስ ነው። ከዚያ በኋላ ይረሳዋልና እስከማይለወጥበት ጊዜ ድረስ ብቻ ማመን ነው።

**(አዲስ ዘመን ታህሳስ 26 ቀን 1963 ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ




## በኢኳዶር "ዋና ተፈላጊ" ወንጀለኛ ከእስር ቤት ጠፋ

በኢኳዶር የሎስ ቾነሮስ የወንጀል ቡድን መሪ እና ዋና ተፈላጊ የሆነው እስረኛ ታስሮ ከነበረበት እስ ርቤት ማምለጡን ባለሥልጣናት ተናገሩ። የሀገሪቱ ፖሊስ አዛዥ ጀነራል ሴዛር ዛፖታ እንደተናገሩት ጦሩ በጉያቁሊ እስር ቤት ከነበሩት ወንጀለኞች ውስጥ አንዱ መጥፋቱን አረጋግጠዋል።

ዛፖታ ጠፋ የተባለውን እስረኛ ስም ባይጠቅሱም፣ የዐቃቤ ሕግ ቢሮ ግን የሎስ ቾነሮስ ቡድን መሪ አዶልፎ ማሲያስ እንዴት እንደጠፋ ምርመራ ይካሄዳል ብሏል። ማሲያስ የእፅ ዝውውርን እና ግድያን ጨምሮ በተመሠረተበት በርካታ ክሶች በ2011 ለ31 ዓመታት ተፈርዶበት ነበር።

የሀገሪቱ ባለሥልጣናት ሎስ ቾነሮስን ግድያ፣ እፅ ዝውውር እና ሌሎች ወንጀሎችን በመፈጸም ይከሱታል። በኢኳዶር እስር ቤቶች ተቃናቃኝ የወንጀል ቡድኖች ብዙ ጊዜ የሚደባደቡ ሲሆን ከ2021 ወዲህ 400 እስረኞች ሞተዋል ሲል አል ዓይን ዘግቧል።

በርካታዎቹ የኢኳዶር ማረሚያ ቤቶች ከፉኛ የተጨናነቁ ሲሆን ባለሥልጣናቱ የተቀናቃኝ ቡድን አባላትን ለመለየትም ፈተና ገጥሟቸዋል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በሀገሪቱ ወሮበላ ቡድኖች መካከል በተቀሰቀሰ ግጭት በመቶዎች የሚቆጠሩ እስረኞች ተገድለዋል።

ኢኳዶር በደቡብ አሜሪካ ሰሜናዊ ምዕራብ ክፍል የምትገኝ ሲሆን በሰሜን በኮሎምቢያ፣ በምሥራቅ ፔሩ እና በምዕራብ የፓስፊክ ውቅያኖስ ያዋስኗታል።



## ለታይዋን ከተደረገ የጦር መሣሪያ ሽያጩ ጋር በተያያዘ ቻይና በአምስት የአሜሪካ ድርጅቶች ላይ ማዕቀብ ጣለች

አሜሪካ ለታይዋን ካካሄደችው የጦር መሣሪያ ሽያጭ ጋር በተያያዘ በአምስት የምዕራባውያን የመከላከያ ድርጅቶች ላይ ማዕቀብ እንደምትጥል ቻይና አስታውቃለች። መግለጫው የተሰጠው ታይዋን ከቀናት በኋላ ፕሬዚዳንታዊ እና የፓርላማ አባላት ምርጫን ለማድረግ በምትዘጋጅበት ወቅት ነው ።

የአሜሪካ ጦር መሣሪያ ለታይዋን መሸጥ በቤጂንግ እና በዋሽንግተን መካከል ተደጋጋሚ የውጥረት ምንጭ ነው። ቻይና ታይዋንን እንደ አንድ ግዛቷ ትመለከታለች፤ የታይዋን መንግሥት ግን ይህንን ውድቅ ያደርገዋል። ባለፈው ወር የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የታይዋንን የታክቲካል መረጃ ሥርዓት ለመጠበቅ የሚረዳ የ300 ሚሊዮን ዶላር የመሣሪያ ሽያጭ አጽድቋል።

የቻይናው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እሑድ ዕለት በሰጠው መግለጫ እንዳስታወቀው ማዕቀቡ "ዩናይትድ ስቴትስ ለወሰደቻቸው የተሳሳቱ እርምጃዎች ምላሽ እንዲሆን ነው።"በቅርቡ የተካሄደው የጦር መሣሪያ ሽያጭ የቻይናን ሉዓላዊነት እና ደኅንነት በእጅጉ ከመጉዳት ባለፈ በአካባቢው ያለውን ሠላም እና መረጋጋት ይጎዳል ብሏል።

ማዕቀብ የተጣለባቸው ኩባንያዎች ቢኤኢ ሲስተም ላንድ ኤንድ አርማመንት፣ አሊያንት ቴክሲስተምስ ኦፕሬሽን፣ ኤሮቫይሮንመንት፣ ቪያሳት እና ዳታ ሊንክ ሶሉሽንስ የሚባሉ ናቸው። ቻይና የኩባንያዎቹን ንብረት ከማገድ ባለፈ በቻይና ያሉ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ከእነሱ ጋር እንዳይገናኙ ታግዳለች ሲል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታውቋል።

ደሴቲቱ ከቻይና ጋር ያላትን ግንኙነት ሊቀይረው ከሚችለው ምርጫ በፊት ቤጂንግ፣ በታይዋን ላይ ጫናዋን አሳድጋለች። ፕሬዚዳንት ዢ ጂንፒንግ በዓመታዊው የአዲስ ዓመት ዋዜማ ንግግራቸው ታይዋን ከቻይና ጋር "በእርግጠኝነት ዳግም ትዋሓዳለች" ሲሉ በድጋሚ ተናግረዋል።

ባለፈው ዓመት ካስተላለፉት ጠንከር ባለ መልኩም ታይዋን "የትልቁ ቤተሰብ" አካል መሆኗን ተናግረዋል። 23 ሚሊዮን ሕዝብ ያላት ደሴት ውሎ አድሮ በቤጂንግ ቁጥጥር ስር እንደምትሆን ቤጂንግ ታምናለች። ታይዋን ራሷን ከቻይና የተለየች፣ የራሷ ሕገ መንግሥት እና በዴሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጡ መሪዎች እንዳላት አገር ትቆጥራለች ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

# ስፖርት

## ኢትዮጵያዊያኑ አትሌቶች የውድድር ዓመቱን በስኬት ጀምረዋል

ብርሃን ፈይሳ

በአዲሱ የአትሌቲክስ የውድድር ዓመት የመጀመሪያ ሳምንት በመላው ዓለም በርካታ የጎዳና ላይ ሩጫዎች ተከናውነዋል። በተለያዩ ርቀቶች በተደረጉት በእነዚህ ውድድሮች ላይም እንደተለመደው በርካታ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ተካፍለው ውጤታማ መሆን ችለዋል። ከእነዚህ መካከል አንዱ የቻይናው የዚመን ማራቶን ሲሆን፤ በሁለቱም ጾታዎች አሸናፊ በመሆን ውጤታማ ጅማሬን አስመዝግበዋል።

የዓለም አትሌቲክስ የፕላቲኒየም ደረጃ ከሰጣቸው ዋናዎቹ የማራቶን ሩጫዎች መካከል አንዱ እና በዓመቱ የመጀመሪያው በሆነው በዚህ ውድድር ሁለተኛው ፈጣን ሰዓትም ተመዝግቧል። የሩጫው አሸናፊ የሆነው ኢትዮጵያዊው አትሌት አሰፋ ቦኪ ፈታኝ በነበረው ውድድር ተፎካካሪዎቹን በጥቂት ሰከንዶች ብቻ በመቅደምም ነው ባለ ድል የሆነው። አትሌቱ የገባበት ሰዓት 2:06:46 ሲሆን፤ እአአ በ2015 በኬንያዊው አትሌት ከተመዘገበው የቦታው ክብረወሰን 27 ሰከንዶችን ብቻ የዘገየ ነው። ሁለተኛ ደረጃን የያዘው ኬንያዊ አትሌት ፍሊክስ ኪርዋ 2:06:52 የሆነ ሰዓት ሲያስመዘግብ፤ ሞሮኳዊው ኦትማን ኤል ጎምሪ ደግሞ 2:07:18 በሆነ ሰዓት ሶስተኛ ሆኗል። በዚህ ውድድር ተሳታፊ የነበሩት ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች አዳነ ከበደ እና አለነ መኮንን በበኩላቸው አራተኛና አምስተኛ ደረጃን በመያዝ ውድድራቸውን አጠናቀዋል።



በዚመን ማራቶን ወንዶች አሸናፊ የሆነው አትሌት አሰፋ ቦኪ



በዚመን ማራቶን የሴቶች አሸናፊዋ አትሌት በቀለች ጉደታ

በሴቶች መካከል በተደረገው ውድድር ደግሞ በግማሽ ማራቶን የምትታወቀው አትሌት በቀለች ጉደታ አሸናፊ ልትሆን ችላለች። የ26 ዓመቷ አትሌት ርቀቱን 2:22:54 በሆነ ሰዓት ስትሸፍን የግሏን ፈጣን ሰዓትም አሻሽላለች። ሁለት ደቂቃዎችን ዘግይታ የገባችው ሞሮኳዊቷ ፋጢማ ኢዛህራ ሁለተኛ፤ እንዲሁም ቻይናዊቷ ዣንግ ዴሹን ደግሞ ሶስተኛ ሆነዋል። ሌሎቹ ኢትዮጵያዊያን አያና ሙሊሳ እና ጉልሜ ጫላ ደግሞ አራተኛ እና ስድስተኛ ደረጃን ይዘዋል።

በሳምንቱ መጨረሻ ከተካሄዱ የማራቶን ውድድሮች መካከል አንዱ የዱባይ ማራቶን ነው። ለዓመታት የዱባይ ማራቶንን በበላይነት ማጠናቀቅ የቻሉት ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ደግሞ ዘንድሮም እንደተለመደው ተከታትለው በመግባት በአሸናፊነት መፈጸም ችለዋል። በውድድሩ ታሪክ የላቀ የማሸነፍ ልምድ ያላቸው ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች አይበገሬነት በሁለቱም ጾታ የተረጋገጠ ሲሆን፤ በተለይ በሴቶች በኩል የቦታውን ክብረወሰን በመሰበሩ በሁለቱም ጾታዎች የፈጣን ሰዓት ባለቤቶች ኢትዮጵያዊያን ሆነው ሊመዘገቡ ችለዋል። ሜዳማ በሆነ ስፍራ የሚካሄደው የዱባይ ማራቶን ፈጣን ከሆኑ የጎዳና ሩጫዎች መካከል አንዱ በመሆኑ በአትሌቶች በእጅጉ ተመራጭ መሆኑ ይታወቃል። በመሆኑም ታዋቂ እና ጀማሪ አትሌቶች በዚህ ውድድር በስፋት ተሳታፊዎች ናቸው። በአዲሱ የፈረንጆቹ ዓመት የመጀመሪያ ሳምንት በተካሄደው በዚህ ውድድር ለመጀመሪያ ጊዜ የተሳተፈችው አትሌት ትዕግስት ከተማ 2:16:07 ሰዓት በመግባት ነው የርቀቱን ክብረወሰን ከኬንያዊቷ አትሌት ሩት ቺህፒጌቲች እጅ ልትረከብ የቻለችው።

ኬንያዊቷ አትሌት እአአ በ2019 ውድድሩን 2:17:08 በሆነ ሰዓት በመሸፈኗ የፈጣን ሰዓት ባለቤት ብትሰኝም፣ ከአንድ ደቂቃ በላይ ፈጥና በገባችው 25 ዓመቷ ኢትዮጵያዊት ብልጫ ተወስዶባታል። ትዕግስት በዚህ ሰዓት በማራቶን ታሪክ ስምንተኛዋ ፈጣን ሴት ሯጭ ስትሰኝ የ80ሺ ዶላር ተሸላሚም ሆናለች። አምና በዚህ ውድድር ሁለተኛ የወጣችውና በበርካታ ማራቶኖች ተሳትፎዋ የምትታወቀው ሌላኛዋ ኢትዮጵያዊት አትሌት ሩቲ አጋ ዘንድሮም ሁለተኛ ደረጃን ይዛለች። አትሌቷ ከትዕግስት በሁለት ደቂቃዎችም ነው ዘግይታ የገባችው። በዚህ ውድድር ዘንድሮም ለሁለተኛ ጊዜ አሸናፊ ትሆናለች የሚል ቅድመ-ግምት ያገኘችው አትሌት ደራ ዲዳ ደግሞ ሶስተኛ ደረጃን ይዛለች። እስከ 12ኛ ያለው ስፍራም ከሁለት የሌላ ሃገር አትሌቶች ጣልቃ ገብነት በቀር በኢትዮጵያዊያን የተያዘ ሆኗል።

በተመሳሳይ በወንዶች በኩልም ኢትዮጵያዊያኑ ተከታትለው በመግባት የበላይነቱን ሲቆጣጠሩ አትሌት አዲሱ ጎበና የሃገሩን ልጆች በማስከተል አሸናፊ ሊሆን ችሏል። በጠንካራ ፉክክር መታጀቡን የሚያመለክተው ውድድሩ እጅግ ተቀራራቢ የሆነ ሰዓት የተመዘገበበት ሲሆን፤ 2:05:01 የሆነው ሰዓት አትሌቱን ባለድል ሊያደርገው ችሏል። በ19 ሰከንዶች ብቻ የተቀደመው አትሌት ለሚ ዱሜቻ ሁለተኛ ደረጃን ሲይዝ፤ ደጀኔ መገርሳ ደግሞ በ41 ሰከንዶች ዘግይቶ ሶስተኛ ሆኗል። በርካታ ቁጥር ያላቸው ሌሎች ኢትዮጵያዊያንም ተከታትለው በመግባት የውድድሩን ፍጹም የሆነ የበላይነት ተቆጣጥረዋል።

ከሳምንት በፊት በስፔን በተካሄደ የ10 ኪሎ ሜትር ውድድር ላይ አሸናፊ የነበረው ወጣት አትሌት በሪሁ አረጋዊ በድጋሚ ሌላኛው የዙር ውድድር ላይም አሸናፊ በመሆን ድሉን ማጣጣም ችሏል። በስፔን እየተካሄደ በሚገኘውና በዓለም አትሌቲክስ የወርቅ ደረጃ በተሰጠው የሃገር አቋራጭ ቱር ውድድር ላይ በመሳተፍ ላይ የሚገኘው አትሌቱ በጭቃማውና ፈታኝ በሆነው ውድድር ሳይረታ 30:34 የሆነ ሰዓት በማስመዝገብም ነው አሸናፊ የሆነው።


## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

የፍ/ባለመብት አሊ መሀመድ እና በፍ/ባለዕዳ አቶ ደመረ ተፈራ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 284578፣276112 በ07/11/2014 ዓ.ም 08/7/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በሀዋሳ ከተማ መናኸሪያ ክ/ከተማ ጉዊ ቀበሌ ውስጥ የሚገኘው ይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቁጥር 00347 በልዩ ቁራሽ መሬት መለያ ኮድ SD001020 907095 በወ/ሮ ወሰነች ቶማስ እና በአቶ ደመረ ተፈራ ስም የተመዘገበ ይዞታው ስሪት ሊዝ የሆነ 200 ካ/ሜ መኖሪያ ቤት ይዞታ በቀድሞ የመሬት ልማት ልኬት 200 ካ/ሜ ሲሆን በአዲሱ ካዲስትር በተረጋገጠው ልኬት ትክክለኛ 198.21 ካ/ሜ ሆኖ ይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው በዚሁ መሆኑ

ታውቆ የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 4,200,900.52 (አራት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ ዘጠኝ መቶ ብር ከሃምሳ ሁለት ሳንቲም) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ጥር 29 ቀን 2016 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ5፡30 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል።

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ጀምሮ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ባለበት ቦታ ድረስ በመውሰድ መጐብኘት የሚችሉ ሲሆን፤ እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን መነሻ ግምት 1/4 ኛውን በንግድ ባንክ በተረጋገጠ c.P.O ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ c.P.O የሚያመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በፍ/አ/ዳ/ ስም C.P.O አሰርቶ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብቻ ሙሉ ገንዘቡን በ15 ቀን ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት። የፍ/አ/ዳይሬክቶሬት ንብረቱን በህጋዊ መንገድ በሀራጅ ስለመሸጡ ለሚመለከተው አካል ማስረጃ ከመጻፍ ባለፈ ስም የማዛወር ግዴታ የሌለበት መሆኑን እንገልጻለን።

**በፌዴራል ፍርድ ቤቶች**
**የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት**

## የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

የአመልካች ስም፡ Pfizer Jtalia S.R.L አድራሻ፡ Via lsonzo 71, 04100, Latina, ltaly
2. የማመልከቻ ቀን 13/06/2023 እ.ኤ.አ
3. የማመልከቻ ቁጥር፡ FTM/14279
4. የንግድ ምልክቱ መግለጫ፡ የቃል
5. የንግድ ምልክት PHARMORUBICIN
6. ቀለም፡ ጥቁር እና ነጭ
7. ዓለም አቀፍ ምድብ፡ 05
8. ምርቶች፡ ለካንሰር ህክምና የመድኃኒት ዝግጅቶች

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ስለሆነም ማንኛውም ግለሰብ ወይም የህግ ሰውነት ያለው ተቋም ከባለቤቱ ፍቃድ ውጪ በዚህ ምልክት የሚጠቀም ወይም አስመስሎ በሚሰራ ላይ በህግ ክስ ይመሰረትበታል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**
**ADDIS ZEMEN VOl-LXXXIII No-120 30/4/2016 (9/1/2024)**

የባለንብረቱ ስም መኳንንት ገበይ ምክሩ የሰሌዳ ቁጥር 01-21644 አማ የተሽከርካሪ ዓይነት ባለሶስት እግር ተሽከርካሪ ሞዴል RE- 45 የተሽከርከሪው የአገልግሎት ዓይነት ለከተማ ታክሲ የሞተር ቁጥር AZZWGD65901 የሻንሲ ቁጥር MD2A25BZ3GWD58463 የተሽከርካሪው የመጫን አቅም 3 ሰው የአመታዊ የምርመራ ቀን 28/04/2016 ዓ.ም. ከላይ የተጠቀሰው ባለንብረት ሰሌዳ የጠፋ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም ይህን ሰሌዳ ወድቆ፣ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**ባህርዳር ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም እስማኤል አሸም ከሊፋ የሠሌዳ ቁጥር አአ 03-01-05080 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር 35310114273269 ሞዴል 911 የሞተር ቁጥር 352-906-10-428601 የሊብሬ ቁጥር 425416 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፉብኝ ብለው በ26/4/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅ/ጽ/ቤት**

በከሳሽ ወ/ሮ ወይንሸት ውበቱ እና በተከሳሽ ኢዳሪኦን ግሩፕ ሊሚትድ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሣሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ 1ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ የጋዜጣ ማስታወቂያ አውቀው መልስዎን በጽሁፍ ለ07/05/2016 ዓ.ም. በ5፡00 ሰዓት እንዲያቀርቡ ፍ/ብቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ**